# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

አማርኛ ቋንቋ፣ሥነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

## የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና ውጤት ተዛምዶ

(በሀዋሳ ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)

በ

ንፁህ ሞላ

መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

# የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና ውጤት ተዛምዶ

በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የተሰራ ጥናት

በ

ንፁህ ሞላ

መስከረም 2016 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ሙላት አስናቀ ዶ/ር --------------------------------

አማካሪ ፊርማ

------------------------- ---------------------------------

ፈታኝ ፊርማ

## ማውጫ


ምስጋና ... iii

አጠቃሎ ... iv

ምዕራፍ አንድ ፦ መግቢያ ... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ... 1

1.2. የጥናቱ ንድፈ ሀሳብ ... 3

1.3 የጥናቱ መነሻ ችግር ... 4

1.4. የጥናቱ ዓላማ ... 5

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ... 6

1.6.የጥናቱ ወሰን ... 6

1.7. የጥናቱ ውስንነት ... 7

1.8. የጥናቱ ቁልፍ ቃላት ... 7

ምዕርፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ... 9

2.1. የአመለካከት ፅንሰ ሀሳብ ... 9

2.2. የአመለካከት ባህርያትና ምንነት ... 10

2.3. በአመለካከት ላይ ተጽኖ የሚያሳድሩ ተላዉጦዎች ... 11

2.4. የወላጆችና የማህበረሰቡ ተፅዕኖ ... 12

2.5. የተማሪ ጓደኛ የሚያሳድረውተፅዕኖ ... 14

2.6. የመማሪያ መጽሐፍ ተፅዕኖ ... 15

2.7. አመለካከት ከውጤት ጋር ያለው ዝምድና ... 17

2.8. የቀደምት ጥናት ቅኝት ... 21

ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ ... 26

3.1 የጥናቱ ንድፍ ... 26

3.2 የናሙና አመራረጥ ... 26

3.3 የጥናቱ ተሳታፊዎች ... 26

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ... 27

3.4.1 የፅሁፍ መጠይቅ ... 27

3.4.2 ሰነድ ፍተሻ ........................................................................................ 28
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........................................................................................ 28
3.6. ጥናቱ የተሰራበት ስነ-ምግባር፡ ........................................................................................ 29
ምዕራፍ አራት፡-የውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........................................................................................ 30
4.1. የተጠኚዎች አጠቃላይ ዳራ ........................................................................................ 30
4.1.1.ፆታ ........................................................................................ 30
**4.2 የውጤት ትንተና** ........................................................................................ 30
4.2.1 **ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋናትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ትንተና** ........................................................................................ 32
4.2.2. የተማሪዎች አመለካከት በፆታ ........................................................................................ 34
4.2.3. አካዳሚያዊ ውጤት ትንተና ........................................................................................ 35
4.2.4.የተማሪዎች ውጤት በፆታ ........................................................................................ 36
4.2.5.**በአመለካከትና የፈተና ውጤትመካከል ያለው ተዛምዶ** ........................................................................................ 37
**4.3. የጥናቱ ማብራሪያ** ........................................................................................ 39
ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ ........................................................................................ 42
**5.1. ማጠቃለያ** ........................................................................................ 42
**5.2. አስተያየት** ........................................................................................ 44
**ዋቢ መፅሃፍት** ........................................................................................ 46
**የፅሁፍ መጠይቅ** “........................................................................................ 50
**አባሪዎች** ........................................................................................ 54

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ በትምህርት ላይ እንዳለሁ ከገጠመኝን ተደጋጋሚና ውስብስብ የጤና ችግር አሳልፎ ለዚህ ደረጃ ያበቃኝን እግዚአብሄርን አመሰግናለሁ፡፡

በመቀጠል ይህ ስራ የተሟላ ይሆን ዘንድ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ስህተቴን ነቅሰው በማውጣትና በማስተካከል ተገቢውን አስተያየት በመስጠትና ጊዜዬን በአግባቡ እንድጠቀም ፈጣን ምላሽ በመስጠት ለአገዙኝ  ለአማካሪዬ ለዶክተር ሙላት አስናቀ እጅግ በጣም ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡እንዲሁም ይህን ጥናት እንድሰራ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በማስከተልም ከጎኔ በመሆን ላበረታቱኝና በየትኛውም ሰዓት ድጋፋቸው ላልተለየኝ ለውድ ቤተሰቦቼ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በመጨረሻም ይህ ስራ የተሳካ እንዲሆን እገዛ ላደረጋችሁልኝ ጥናቱን የሰራሁበት ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንና መምህራን ፣እንዲሁም ሌሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የበኩላችሁን ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ ጓደኞቼ በሙሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሀዋሳ ምስራቅ ጮራ ት/ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ሲሆን ጥናቱ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው ። ይህን ዓላማ ለማሳካት ይረዳ ዘንድ በ2015 ዓ.ም በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል ከሚማሩና አፍ መፍቻቸው ሲዳምኛ ከሆኑ 295 ተማሪዎች 35% በመውሰድ በአጠቃላይ 103 ተማሪዎች በእኩል ዕድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ስልት በተጠኚነት ተመርጠዋል። የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሁፍ መጠይቅና የሰነድ ፍተሻ ነው። የመረጃ መተንተኛዎቹም የተዛማች ስሌትና የአስተማማኝነት ግንኙነት መለኪያ ስልቶች ናቸው።የተማሪዎች አጠቃላይ አመለካካት አማካይና የአንደኛ ወሰነ ትምህርት በክፍል መምህራን የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች አማካይ ውጤት ያለው ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ቀመር መሰረት በኮምፒዩተር ኤስ ፒ ኤስ ኤስ ተሰልቶ ቀርቧል ። ስሌቱም ያሳየው በአመለካከትና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ መኖሩን ነው። የሁለቱ ተላውጦዎች ዝምድና መጠን መካከለኛ (0.456) መሆኑን የተገኘው ውጤት አረጋግጧል ። በዚሁ መሰረት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው መለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩንና ይህ ዝምድና ከፆታ አንፃር ልዩነት ይኖረው እንደሆነ በዚሁ በፒርሰን ተዛምዶ ተሰልቶ መጠኑ የተገለፀ ሲሆን ውጤቱ ያመላከተው ከፆታ አንፃር ልዩነት የሌለው መሆኑን ነው ። ስለሆነም የተማሪዎች ውጤት ማነስ ከአመለካከት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በአመለካከት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ የጥናቱ ውጤት ያመላክታል።

# ምዕራፍ አንድ ፡- መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አመለካከትና የቋንቋ ትምህርትአብዛኛውን ጊዜ በትምህርት ቤት የተለመዱና ከትምህርት ጋር የተያያዘ እሳቤ ያላቸው በመሆኑ አንድ ተማሪ በታላሚው ቋንቋ ላይ በጎ አመለካከት ካለው ጥሩ ውጤት ያስመዘግባል በጎ ያልሆነ አመለካከት ካለው ደግሞ ዉጤቱ ተቃራኒ ይሆናል የሚሉ አገላለጾች የሚዘወተሩ ናቸው፡፡ ሆኖም Nunan and Lanbert(1996) ይህንን አስመልክተዉ ሲገለጹ ‹‹አመለካከት በቋንቋ ትምህርት ተስተምሮ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀጥተኛ ሳይሆን፤ተፅዕኖ ሊያመጣ ወደሚችል ማነቃቂያ ወይም ተነሳሽነት የሚመራ ነው፡፡

እንደ Rosenberg and Howland (1980፡6) አመለካከት እንዲከሰት ወይም ወደ ተነሳሽነት እንዲለወጥ የሚያስችለው ዋናው ሰበብ በግልጽ በሚታየዉ በተተኳሪ ነገር ወይም ክስተት ላይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተላውጦዎች ለምሳሌ የቋንቋው ተማሪና ቋንቋ ትምህርቱ ውስብስብነትና ስነ-ልቦናዊ አስተሳሰብ እንዲሁም ፖለቲካዊ ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አመለካከት የሚመነጩ ተፅዕኖዎች ናቸው ብለዋል፡፡

በቋንቋ ትምህርት ሂደት በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ክንውን ወቅት ተማሪውን የተለያዩ ማህበራዊ፣ ስነ ልሳናዊ፣ እና ስነ ትምህርታዊ ችግሮች ይገጥሙታል፡፡ በትምህርት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱት በርካታ ተላውጦዎች መካከል አንዱ ተማሪው ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያለው አመለካከት ነው፡፡ ተማሪው ከክፍል ውጭም ሆነ ዉስጥ የሚገጥሙት ችግሮች ከአመለካከት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት አላቸው፡፡ ለትምህርት የቀረበ ቋንቋ፣ የትምህርት ስርዓቱ፤ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ መምህሩ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች፣ የተማሪው ባልደረቦች፣ ወላጆችና ማህበረሰቡ ተማሪው ለትምህርቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ

አመለካከት እንዲዳብር ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች ዉስጥ በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው (Harmer ,1990፡4-25,Rivers, 1981:132)::

አጥኚዋ ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ እንደተረዳችው ለትምህርት የቀረበው ቋንቋ፣ የትምህርት ስርዓቱ፣የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ መምህሩ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች፣ የተማሪው ባልደረቦች፤ወላጆችና ማህበረሰቡ የተማሪው አመለካከት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሆኖ እንዲዳብር አስተዋጽኦ እንዳላቸው ነው፡፡

አሉታዊ አመለካከት ለተማሪዎች ውጤት ዝቅ ማለት መንስኤ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሆነ ለመለካትና ይህ አመለካከት ከውጤት ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች አመለካከት አሉታዊ ከሆነ ወደ አዎንታዊነት መለወጥ የሚቻልበትን ስልት መፈለግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ማለት የትምህርት ስርዓትን፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ከተማሪው ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ማድረግና አመለካከታቸውን አዎንታዊ ማድረግ በሚቻልበት አካሄድ በማቅረብ መለወጥ ይቻላል (Dubin 1986:15, Gardner 1985:89)::

ከላይ እንደተገለፀው የተማሪውን አመለካከት አዎንታዊ ለማድረግ ከሚረዱ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ለቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ ተብለው የሚዘጋጁ መጽሐፍት ተማሪው ቋንቋውን ለምን ዓላማ እንደሚማር ፍላጎቱ ምን እንደሆነ በትምህርትነት ለቀረበው ታላሚ ቋንቋ ትምህርት ያለውን አመለካከት የወጣበትን ማህበረሰብ ከማንነትና ፍላጎት በአማካይ ማወቅ በሚያስችሉ የጥናት መረጃዎች ላይ ተመስርተዉ መሆን ይገባቸዋል (Dubin 1986, Richards 1987)፡፡ ከማህበረሰብ አንጻር ሲታይ ቤተሰብ የመጀመሪያውትምህርት ቤት ነው፡፡ በዚህ የመማር ሂደት ውስጥ ልጆች የወላጆቻቸውን መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎቶች የሚቀስሙበትና የራሳቸውን

አመለካከት የሚፈጥሩበት እርከን ነው ማለት ይቻላል። Spoiskey(1989) ይህንን አስመልክቶ ሲያብራሩ የቋንቋ መማር ማስተማር ተግባር ከማህበራዊ አውድ ውጭ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። በማህበራዊ አውድ ከሚጠቀሱ ተላውጦዎች መካከል ቤተሰብ፣ አካባቢያዊ ትምህርትቤት፣ መንግስት ይገኙባቸዋል ብለዋል። ለምሳሌ:-ወላጆች ለልጆቻቸው ታላሚውን ቋንቋ እንዲማሩ የማበረታታትና በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ያለውንም ጥብቅ ግንኙነት በተመለከተ በርካታ የውጭ ሰዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት አስመልክተዉ ጥናት አድርገው ዝምድናቸውን አረጋግጠዋል። ይህም ማለት አዎንታዊ አመለካከት ከከፍተኛ ውጤት ጋር አሉታዊ ደግሞ ከዝቅተኛ ውጤት ጋር እንደተጣመረ አሳይተዋል( Gardner,1985:90):: ይሁን እንጂ አመለካከት ከውጤት ጋር ግንኙነት እንደሌለው ሌሎች ምሁራን በጥናታቸው አረጋግጠዋል።

አጥኚዋ ከላይ የተዘረዘሩትን የጥናት ነጥቦች እንደመነሻ በማድረግ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የውጤት ተዛምዶ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ሞክራለች።

## 1.2. የጥናቱ ንድፈ ሀሳብ

ይህ ጥናት ማንሱር (1993) ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር የቋንቋ አመለካከትና ተነሳሽነት ሚና በሚል ባደረገችው ሰፊ ጥናት ባስቀመጠችው ንድፈ ሐሳቦች ላይ የተመሰረተ ነው።የማንሱር ስራ የመነጨው ላምበርት (1974 በጋርድነር፣ 1985) ካቀረበው የማህበራዊ ስነ ልቦና ሞዴል ጥናት ነው። በዚህ ሞዴል መሰረት የተማሪው ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት የሚወሰነው ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋውን ለመማር ባለው አመለካከት ላይ ነው።Lambert (1974, in Gardner, 1985) የተማሪው ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት የሚወሰነው ተማሪው በቋንቋው ላይ እና ቋንቋውን ለመማር ባለው አመለካከት ላይ ነው በማለት አብራርተዋል::

ይህ ጥናት Lambert (1974, in Gardner, 1985) and Mansoor (1993), ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ተማሪው ያለው አዎንታዊ አመለካከት ቋንቋውን በብቃት ለመማር እንደሚያስችለው እያንዳንዳቸው አጉልተው ባሳዩት ፅንሰ-ሃሳባዊ ማዕቀፍ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ መነሻ ችግር

በሀገር ውስጥ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ስላላቸው አመለካከት ጥናት ካቀረቡ ምሁራን ውስጥ እሸቱ (1997)፣አበበ (2003)፣ፀጋዬ (1996)፣ተዋበች (2003)፣፣ታሪኩ (1988)፣ወንደሰን (1989) ለተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች በማሚያነት ያቀረቧቸው ፅሁፎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከነዚህም ምሁራን እሸቱ (1997)፣አበበ (2003)፣ተዋበች (2003)፣ታሪኩ (1988)፣ወንደሰን (1989) በጥናቶቻቸው የታቀፉት ተማሪዎች ለቋንቋውና ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ሲያረጋግጡ ፀጋዬ(1996) አሉታዊ አመለካከት እንዳስመዘገቡ አሳይቷል፡፡እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጥናቶች ከጥናቱ መነሻ ችግር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማመላከት እንጂ ጥናቶቹ የተሰሩበት ዓላማና የተከተሉት ስነ ዘዴዎችና የተገኙ ውጤቶች በክለሳ ድርሳናት ስር ቀርበዋል፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት የሀገር ውስጥ ስራዎች ጋር ሲታይ ተማሪዎች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ከማጥናት አንጻር የሚቀርብበት ሲሆን አመለካከት ከውጤት ጋር ያለውን ዝምድና ከማነጻጸር አኳያና በአማርኛ አፋቸውን ያልፈቱ ሆነው እንደሁለተኛ ቋንቋቸው አድርገው በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ይበልጥ ከተዋበችና ወንደወሰን ሰራ ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከብሄረሰቡና ከቋንቋው ቤተሰብ አንጻር የተለየ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አጥኚዋ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና የሚል ጥናታዊ ርዕስ ለመምረጥ ምክንያት የሆናት በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ

ተማሪዎችን ለዘጠኝ አመት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ስታስተምር አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ተመልክታለች፡፡ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት ምናልባት ለውጤታቸው ዝቅተኛ መሆን መንስዔው አመለካከታቸው ይሆን? ከሆነስ መፍትሔ አይገኝለትምን? የሚሉ ጥያቄዎችን እንድታነሳ ተገዳለች፡፡ በተጨማሪ ሌሎች መምህራን የተማሪዎቹን የቋንቋ አመለካከት በመደበኛና በዕለት ተዕለት ሕይወት መስተጋብር አሉታዊ የአማርኛ ቋንቋ አመለካከታቸውን አግዝፈው ሲያወሱት አጥኚዋ አድምጣለች፡፡ በመሆኑም በተለያዩ በቋንቋ ተመራማሪዎች ከተገለጹት የአፍ መፍቻቸው ሲዳምኛ የሆኑ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤት ዝምድና ለመለየትና መፍትሔ ለማምጣት የተሰሩ ጥናቶችአጥኚዋስላላጋጠማት ለዚህ ጥናት እንድትነሳሳ አድርጓታል ፡፡በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ በታች የቀረቡትን ሶስት ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡

1. በሲዳምኛ ቋንቋ አፈፊት የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
2. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፆታ አንጻር ልዩነት እንዳለው መመርመር
3. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባላቸው አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ዝምድና ይኖረዋል?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በሲዳምኛ ቋንቋ አፈፊት የሆኑ የአስረኛክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ሲሆን ከዚህ አብይ ዓላማ የመነጩ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በሲዳምኛ ቋንቋ አፊፊት የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት መመርመር፡፡
2. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፆታ አንጻር ልዩነት እንዳለው መመርመር
3. በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ምን ዓይነት ዝምድና እንዳለ መፈተሽ

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

1. በሲዳማ ክልል ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት በመለየት ለመፍትሄ እንዲነሳሱ ያደርጋል፡፡
2. መምህራንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ምን አይነት ዝምድና እንዳለ ለመለየት ጠቋሚ በመሆን ያገለግላል፡፡
3. የመርሀትምህርት ነዳፊዎች፣የመማሪያ መጻህፍት አዘጋጆች እንዲሁም የትምህርት ባለሙያዎች በተማሪዎች የሚወደድ የመማሪያ መጽሀፍትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማዘጋጀት ይችሉ ዘንድ ጠቋሚ መረጃ ይሰጣል፡፡
4. ለወደፊት በተቀራራቢ ርዕሰ ላይ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎችእንደ መነሻ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6.**የጥናቱ ወሰን**

ጥናቱ በሲዳማ ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሁሉንም የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አያካትትም ፡፡ በሀዋሳ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከል ምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት10ኛ ክፍል ተማሪዎችን  ዓላማ ተኮር ንሞና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት አጥኚዋ

የጥናቱን መነሻ ችግር ያስተዋለችበት እና የመደበኛ ስራ ቦታዋ በመሆኑ ጥናቱ በዚህ ትምህርት ቤት እንዲወስን አድርጎታል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪዎች በዚህ ትምህርት ቤትበ2015 የትምህርት ዘመን ተመዝግበው የሚማሩ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

ጥናቱም የተማሪዎቹን አመለካከት ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ የሚመረምር ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያላቸውን አመለካከትና በመምህራን ከሚዘጋጀው የአስረኛ ክፍል የአንደኛ መንፈቅ ዓመት የአማርኛ ፈተና ውጤት ጋር የሚነጻጸር ይሆናል፡፡ ይህም በመሆኑ ተማሪን በአንድ የፈተና ውጤት ብቻ ከመፈረጅ ያድን ዘንድ የአንደኛ መንፈቅ ዓመት ዉጤት እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ በተለይ መንፈቅ ዓመቱ ፈተናው የተገቢነት ደረጃው በአማካይ ሲታይ የታቀደውን የዕውቀት ክፍልና ማካተት የሚገባውን ይዘት ሊጠብቅ ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ለማነጻጸሪያነት ተወስዷል፡፡ ጥናቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ሁኔታ እንጂ አመለካከትን የሚወስኑ ተላውጦዎችን አይመለከትም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነት

የተወሰደው የተጠኚ ተማሪዎች የአማሪኛ ፈተና ውጤት የ1ኛ ሴሚስቴር ብቻ መሆኑና የዓመቱን ውጤት የማያጠቃልል መሆኑ እና ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሁሉንም ተላዉጦዎችን አለማንሳቱ የጥናቱ ውስንነት ነው፡፡

## 1.8. **የጥናቱ ቁልፍ ቃላት**

አመለካከት-አንድ ሰው ስለ ቋንቋ የሚኖረው ቀና ወይም ቀና ያልሆነ ውስጣዊ አስተሳሰብ ነው፡፡

ግላዊ አመለካከት- አንድ ሰው በአንድ ወቅት የሚኖረው የራሱ የሆነ ውስጣዊ አስተሳሰብ ነው፡፡

አዎንታዊ አመለካከት-አንድን ነገር የመውደድ፣ የመቀበል፣ የመደገፍ፣ ወዘተ ዝንባሌ ነው፡፡

አሉታዊ አመለካከት-አንድን ነገር የመቃወም፣ የመጥላት፣ የመንቀፍ፣ ወዘተ ዝንባሌ ነው፡፡

ማህበረሰብ- ተማሪው በሚኖርበት ክልል ውስጥ የሚገኙ የቅርብ ሆነ የሩቅ ነዋሪ ሰዎች ናቸው፡፡

ታላሚ ቋንቋ-ተማሪው እንዲማረውና እንዲያውቀው የሚፈለግ ቋንቋ ነው፡፡

# ምዕርፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የአመለካከት ፅንሰ ሀሳብ

አመለካከት የሚለው ቃል የመጣው "አፐተስ" ከሚለው ከላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም ተስማሚነት ወይም መላመድ ማለት ነው ፡፡ በሌላ አገላለጽ ባህሪ ወይም ምግባር ማለትም ነው፡፡ ቋንቋን ለመማር እና ለማዳበር ተማሪዎች ሊኖራቸው የሚገቡ መሰረታዊ ነገሮች ፍላጎት, ተነሳሽነት እና አመለካከት ናቸው፡፡ተማሪዎች ቋንቋን ለማወቅና ለማደበር ከፊለጉ አመለካከት መሰረታዊ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ "አመለካከት" ለሚለው ቃል የተለያዩ ፍቺዎች ያሉት ሲሆን የተለያዩ ባለሙያዎች እንደሚከተለው ተርጉመውታል፡፡አመለካከት ማለት በተሞክሮዎችና በልምዶች ምክንያት የሚፈጠርና የሚገነባ ስሜታዊና አእምሮአዊ ዝግጁነት ሁኔታ ሲሆን በሁሉም ነገሮችና ሁኔታዎች ላይ በሚኖረው የግለሰብ ባህሪያት ላይ ተለዋዋጭ ተፅዕኖ የሚያሳድር ኃይል ነው በማለት ኡምሬ እና ካሚል (2012, ገጽ .106) አብራርተዋል፡፡በሎንግማን መዝገበ ቃላት (2003), አመለካከቶች ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር ወይም ስለ አንድ ሰው ያሉት አስተያየቶች እና ስሜቶች ናቸው ብለዋል፡፡ እነዚህ አመለካከቶች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሞንታኖ እና ካስፐርዚክ (2008, ገጽ 71) አመለካከት የሚወሰነው ባህሪውን በመፈፀም በሚገኙ ውጤቶቹ ወይም ባህሪያት ላይ በሚኖረው የግለሰቡ እምነት (የባህሪ እምነቶች) ላይ ሲሆን የሚለካውም በእነዚያ ውጤቶች ወይም ባህሪያት ግምገማዎች ነው በማለት አብራርተዋል ፡፡ ስለሆነም ባህሪውን በመፈፀም አዎንታዊ ዋጋ ያላቸው ውጤቶች እንደሚመጡ ጠንካራ እምነት ያለው ሰውባህሪውን ማከናወን ለባህሪው አዎንታዊ አመለካከት ይኖረዋል፡፡ በተቃራኒው፣ ውጤቶችን አሉታዊ ዋጋ የሚሰጡ ጠንካራ እምነቶችን የሚይዝ ሰውበባህሪው ምክንያት አሉታዊ አመለካከት ይኖረዋል.፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አሴር እናሲምፐሰን (1994፣ ገጽ 254) አመለካከትለአንዳንድ ነገሮች (ሀሳብ፣ ነገር፣ ሰው፣ ሁኔታ እና ለመሳሰሉት) አወንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ የመስጠት ዝንባሌ ነው በማለትገልፀዋል፡፡

## 2.2. የአመለካከት ባህርያትና ምንነት

የአመለካከትን ምንነት Gardner(1985) እንደሚገልጹት አመለካከት ከሰዎች ውስጣዊ ስሜት፣ እምነት፣ ግምት ወዘተ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በባህሪዉ ዉስብስብ፣ ተለዋዋጭ፣ ረቂቅና ድብቅም ነዉ፡፡ እንዲሁም ከዳበረልምድና ባህሪም ጋር ተጣምሮ የሚገኝና ድብቅም በመሆኑ ስለ አንድ ጉዳይ የሚኖሩ ሰዎች አመለካከት አንዳንድ ጊዜ በቀላሉ ሊገለጽ ሲችል በሌላ ጊዜ ደግሞ ይደበቃል፡፡ ይሁን እንጂ በቀጥታም ከጉዳዩ ጋር ሲገናኝ ከሚችሉ ሁኔታ ጋር አገናኝቶ ሲመረመር ወይም እንዲወጣ የሚገፋፋዉና የሚያነሳሳዉ አጋጣሚ ሲገኝ በቃል በአካላዊ እንቅስቃሴ ወይም በገሃድ ሊታይ በሚችል ድርጊትና የባህሪ ግልጠት ሊታወቅ ይችላል ይላሉ፡፡

ከዚህ ከተጠቀሰዉ ሀሳብ አጥኚዋ እንደተረዳችው አመለካከት ውስጣዊ ስሜት ሆኖ ለረጅም ጊዜ በሰዎች ፀባይ ላይ ተፅዕኖ በማድረግ ሀይሉን መግለጽ የሚችል መሆኑንና ይህም ስሜት በተመሳሳይ መልኩ ከጉዳዩ ጋር ሲገናኝ የባህሪ ለውጥ የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡

ይህንን ሀሳብ በማጠናከር Redy (1995፡11) አመለካከት በአንድ ስነልቦናዊ አካል ላይ ያለ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መጠን ወይም ደረጃ ነው፡፡ ስነልቦናዊ አካል ሲባል ስራ፣ትምህርት፣ግለሰብ፣ተቋም፣ሀሳብ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ አመለካከት አንድ ነገር የመዉደድና የመጥላት፣ ከመደገፍና ከመንቀፍ፣ ከማከናወንና ካለማከናወን፣ ከመቅረብና ከመራቅ፣ ከበጎና በጎካለመሆን እይታ ጋር የተያያዘ ግንዛቤ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

አመለካከት የሚማሩትና በልምድ የሚያዳብሩት እምነት ወይም አተያይ ነዉ፡፡ ይህም ሲባል አመለካከትን የሚማሩት ከደም ጋር የተዋሃደና አብሮ ያደገሳይሆን በልምድና በትምህርት

የሚገኝ ነዉ፡፡ አንድ ሰዉ አንድንነገር የመውደድና የመጥላት ባህሪያት የሚዳብረው በሚያጋጥሙት የተለያዩ ሁኔታዎች መነሻነት ነው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ምንም እንኳን ተማሪው በመጀመሪያ ጥሩ አመለካከት ወይም ከሁለም ገለልተኛ የሆነ ግምት ይዞ ቢቀርብ በክፍል ዉስጥም ሆነ ዉጭ በሚያጋጥሙት ነገሮች አመለካከቱ ሊለወጥ ይችላል፡፡ ይህም ሲባል አመለካከት በሚገጥሙት ነገሮች ሁሉ ሊለወጥ፣ ሊዳብርና ሊሻሻል ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት የአመለካከት ባህሪው ሁኔታዊ እና ተለዋዋጭ ነው ወደማለት ያደርሳል ብለዋል (Fernald,1999፡82)፡፡

አጥኚዋ ከላይ ከተጠቀሰዉ ሀሳብ እንደተረዳችዉ ሰዎች ከዘር ሳይሆን ከአካባቢያቸው የሚያገኙት ትምህርት ለአመለካከት ዕድገት ወይም ለውጥ ቁልፍ ምክንያት መሆኑን ነው)፡፡

## 2.3. በአመለካከት ላይ ተጽኖ የሚያሳድሩ ተላዉጦዎች

በአንድ ልጅ የሕይወት ገጠመኝ ላይ ድርሻ ያላቸዉ ነገሮች በርካታ ናቸዉ፡፡ ከነዚህም ወላጆች፣ መምህራን፣ ጓደኞች ወዘተ ተብለዉ ይጠቀሳሉ፡፡ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ከላይ ከተገለጽት ጋር ከሚያደርጉት ግንኙነት ምክንያት በትምህርታቸዉ ላይ በጎ ይሁን በጎ ያልሆነ አመለካከት እንዲፈጥሩ አስተዋጾ ይኖራቸዋል፡፡ እንደዚሁም ትምህርት ቤት፣ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ የአከባቢ ነዋሪዎችና የእምነት ሁኔታዎች የተማሪዎች አሉታዊ እና አዉንታዊ አመለካከት መዳበር አስተዋጽዖ እንዳላቸዉ ይገልጻል (Malim, 1998:17):

ተማሪዉ በመለደበኛ የትምህርት ስርዓት የሚሰጥ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተጋለጠበት የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ከነዚህም ምክንያቶች ዉስጥ የሚጠቀሰዉ ቋንቋዉ በስርዓተ ትምህርት ዉስጥ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ወይም በሀገሪቱ በአጋጣሚ ወይም በአዋጅ ተመርጦ በትምህርት መስጫ ቋንቋነት በመቅረቡ ብቻ ምርጫ በማጣት ወይም በሁኔታዎች አስገዳጅነት የሚማሩበት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ይህ ከሆነ ተማሪው ትምህርት

ቀስሞ ወደፊት ለሚገጥመው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን ወይም የራሱን የእውቀት ደረጃ አሳድጎ ለመቅረብ የሚችለዉ ሲማር በመሆኑ በቀረበዉ ትምህርት ስርዓት ውስጥ ገብቶ ቋንቋውን ሊማር ግዴታ ይሆንበታል፤ ከነዚህ ውጭ ደግሞ በራሱ አነሳሽነትና ፍላጎት የተለያዩ አላማዎችን ለማሳካት ሲል በውዴታ ሊማረዉ ይችላል። ሁኔታውየትኛውም ይሁን የተማሪው ቤተሰብና የወጣበት ማህበረሰብ ለተማሪው የመማር ፍላጎትና እና አመለካከት አስተዋፅኦአላቸው ብለዋል (Dubin,1990)::

## 2.4. የወላጆችና የማህበረሰቡ ተፅዕኖ

Harmer (1983:4) አገላለጽ ‹‹የተማሪ ወላጆች የታላሚውን ቋንቋ ትምህርት የሚቃወሙና የሚጠሉ ከሆነ የልጁን አመለካከት ወደ አሉታዊ ተጽዕኖ ይወስዱታል፤ በአንጻሩ ወላጆች በቋንቋዉ ላይ ያላቸው ቀና አመለካከት በልጁ ላይ አዎንታዊ አመለካከት ያሳድራል።››

አጥኝዋ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደቻለችዉ ወላጆች ለልጆቻቸው የቋንቋ ትምህርት ለሚኖራቸው ስሜትና አመለካከት ወሳኝ ሚና መጫወት እንደሚችሉ ነዉ።

ተማሪው ወደ ክፍል ሲመጣ የራሱን ዳራ፣ ቋንቋ ወይም የአረፍተ ነጋገር ስልት፣ ችሎታ፣ የስሜት ደረጃ እና ፍላጎት ወዘተ በመያዝ ሲሆን እነዚህን ተላዉጦዎች በቋንቋ ትምህርት ተስተምሮ ዝግጁነት ላይ የራሳቸዉ አስተዋፅኦአላቸው። ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ይዞዋቸው የሚመጣ የተለያዩ አመለካከቶችን የቀሰመው ከወላጆች ነው ለማለት ያስደፍራል። ስለዚህ ወላጆቻቸዉ ቋንቋ ትምህርት የሚገልጻቸው አስተያየቶች ከቋንቋ ትምህርት አመለካከት ጋር በቀጥታ የተዛመዱ መሆናቸውን (Hoover እና Holling, 1995:22) ገልጸዋል።

ወላጆች ለልጆቻቸዉ እንክብካቤ ከማድረግ በተጨማሪ ሀይማኖታቸውን መስተማር፣ ባህልና ሥነ-ምግባርን ማስተላለፍ እና ወደ ፊት ባህሪይ እና ስብዕና መሰረታቸውንም ለማስጨበጥ ደረጃ አላቸዉ። የወላጆች የስብዕና ባህሪያትና አመለካከት የልጆችን ባህሪይ ያርቃል። በመሆኑም

የህፃናት ግንዛቤ አቅጣጫ በወላጆቻቸውተምሳሌትነት የሚቀረፅ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ወላጆች ትልቅና ከፍተኛ ሀይል ያለዉ የትምህርት ተቋም ናቸው ፡፡ በተጨማሪም ተማሪው ያደገበት አካባቢ፣ ጎረቤቶችና አጠቃላይ መህበረሰቡ በህፃናት የስብዕና፣ የባህል፣ የአመለካከትና ግንዛቤ ቀረፃ ላይ ተፅዕኖ አላቸዉ ይላሉ(Roger ,1995:61-70)

ህፃኑ-ስለቤተሰቡ ማንነት ቦታና ደረጃ የባህልና ቋንቋ ልዩነቶችን እንዲሁም አጠቃላይ የስብዕናውን ቀረጻ ከቤተሰቡ ይቀስማል፡፡ እነዚህ የማንነት ጥያቄዎች በአእምሮ ከቆዩ በኋላ በት/ቤት ቆይተው የሚገጥሙት ሁኔታዎች ቀደም ብለውከዳበረው አስተሳሰብ ጋር እየተለዩበት ይሄዱና ራሱን ከወጣበት ህብረተሰብ ቋንቋ አንጻር በመመልከት የሌላዉን ማህበረሰብ ቋንቋ መለየት ይጀምራል ይላሉ (Harmer, 1990:436)::

አጥኚዋ ከዚህ ሀሳብ እንደተረዳችሁ ለልጆች ስብእና ቀረጻ ወላጆች አስተዋፅኦእንዳላቸነው ፡፡

Payne(1997:20) እንደገለጹት ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር የሚያደርጉት የቤተሰብ ተላዉጦዎች የሚከተሉት ናቸዉ በማለት ይዘረዝራሉ፡፡ እነሱም፡- ቤተሰብ ፣ጥሩ ተስተምሮ ፣አሪያ መሆን፣ ለንባብ ጥሩ ዝንባሌ ማሳየት፣ ወላጆች ለቋንቋው ትምህርት ያላቸዉ አመለካከት በጎ መሆን፣ በርካታ የንባብ መጽሐፍ በማቅረብ፣ የወላጆች ድጋፍና የተማሪዉ ትምህርት ላይ ያላው ተሳትፎ የተበረታታ መሆኑ፣ በተለያዩ የተፈጥሮ ጽሑፎች ይዘት በመወያየት የንባብ ተነሳሽነት በመፍጠር፣ ወላጆች በልጆቻቸዉ ላይ የትምህርት ጥራትን አስመልክቶ የሚፈጥሩት በጎ ግምት የሚባሉ ናቸዉ፡፡

## 2.5. የተማሪ ጓደኛ የሚያሳድረውተፅዕኖ

በአንድ ልጅ ሕይወት አቅጣጫ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ወገኖች መካከል አንዱ የተማሪ ጓደኛ ነዉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የማህበረሰቡ አባላት እንደ መሆናቸው መጠን በግላዊና ማህበራዊ አስተሳሰብ ውጪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በመሆኑም በጉርምስና እድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ከክፍል ህግና ስርዓት ያፈነገጠ ባህርይ በማሳየት በመማር ማስተማር ክንዉን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ተሰሚነት ያላቸዉ ከሆኑ በጓደኞቻቸው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ(Hurolck, 1996:397) ገልጿል፡፡የአካባቢ ሁኔታ ፖለቲካዊ ማህበራዊ ጉዳዮች የተማሪው ንቃተ ሂሊና ደረጃ በተማሪው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ያደርሳሉ schonell(1965)

ይህንን ሀሳብ Harmer (1990) እንደሚያስረዱት በቋንቋ ትምህርት ላይ በጎ ያልሆነ እይታ ወይም ጥላቻ ያለባቸው ጓደኞች አመለካከታቸውን ለሌሎች እኩዮቻቸው ለማስተላለፍ ይጥራሉ፡፡ ፍቅርና በጎ እይታ የሞላበት ክፍል ከሆነ ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ላይ በጎ አመለካከት እንዲመሰረት አስተዋፅኦአለው ብለዋል፡፡ በመሆኑም ህፃኑ በእድሜ እኩዮቹ ዘንድ ተቀባይነትና ተወዳጅነት ለማግኘት ሲል የሚወዱትን በመውደድና በመጥላት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከት ይመሰርታል ብለዋል፡፡

ከላይ ከተገለጸው የምሁራን ሀሳብ አጥኝዋ እንደተረዳችው የተማሪ ጓደኞች የማህበረሰቡ ነፀብራቅ እንደመሆናቸዉ መጠን ከማህበረሰቡ ይዘዉት ያመጡትን በጎ አመለካከት እኩያዎቻቸዉ እንዲቀጥሉበት ማድረግ እንደሚችሉና በጎ ያልሆነ አመለካከታቸውን ደግሞ በጓደኞቻቸው ላይ በማንፀባረቅ በመማር ማስተማር ተግባር እና በሌሎችም ማህበራዊ አኗኗር ላይ ተጽእኖ ማሳደር እንደሚችሉ ነዉ፡፡ ይህም የጓደኞች ተጽእኖ የተማሪዎችን አመለካከት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ የማድረግ ሀይል እንዳለዉ የሚገልጽ ነዉ፡፡

## 2.6. የመማሪያ መጽሐፍ ተፅዕኖ

Dubin እና ሌሎች (1986)እንደሚያስረዱት መማሪያ መጽሐፍ ከመዘጋጀቱ በፊት የተማሪውን ማንነት ማለትም ዜግነቱን፣ የትምህርት ዳራውንና የጥናት መስክ ወዘተ የመሳሰለቱ መሰረታዊ ሀሳቦች ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚሁ አንጻር የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ ተማሪዉን ተተኳሪ በማድረግ ለቋንቋ ትምህርት ጥሩ አመለካከትና የመማር አላማ እንዲኖረው የሚያነሳሳ ሆኖ መዘጋጀት አለበት ይላሉ፡፡

ከነዚህ ምሁራን አገላለጽ አጥኝዋ ለመረዳት እንደሞከረችው የቋንቋ ትምህርት በተቃና እና በሰመረ ሁኔታ እንዲካሄድ ብቃት ያላቸው የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት የተማሪዎችን ፍላጎትና አመለካከት መሰረት /አድርገው መዘጋጀት እንዳለባቸውነው፡፡

Shelden (1987) ይህንን ሲያጠናክሩ መማሪያ መጽሐፍት ማሟላት የሚገባቸው ዋና ዋና ጭብጦችን እንደሚከተለው ይጠቁማሉ፡፡ እነሱም፡- የቀረቡት ትምህርት ልምዶች ተማሪው በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጪ ተግባራዊ ሊያደርጋቸውየሚችልባቸው፣ የታላሚውን ቋንቋ ክፍተት ለማዳበር ብቃት ያላቸዉ የትምህርት ይዘቶችና ልምምዶችን ያካተቱ፣ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪው የመማር የምርጫ ነፃነት የሚሰጡና የተማሪውን የመማር ፍላጎት አነቃቅቶ በጥሩ ሁኔታ ሊያሳትፉ የሚችሉ፣ የተማሪውን የዕውቀት ደረጃና ችሎታ የሚጠብቁ ሆነዉ በአማካይ ለሁሉም ተቀራራቢነት ባለዉ ደረጃ የሚጠቁሙ፣ ባዘገጃጀታቸውና በአቀራረባቸዉ ተማሪው ላለበት ሁኔታ፣ ለወጣበት ማህበረሰብና አከባቢ ትኩረት ሰጥተዉ ከታላመው አላማ ማድረስ የሚችሉ ናቸዉ፡፡ ይህንን አስመልክቶ Tarom (1989) እና Harmer (1983) ሲገልጹ መርሀ ትምህርትን ለመቅረጽም ሆነ የመማሪያ መጽሐፍትን ለማዘጋጀትና ለመምረጥ የመረጃ ምንጭ በቅድሚያ ከተቀባዩ ተማሪ መነሳት ይገባል ይላሉ፡፡

ይህም ማለት ተማሪውየቀረበውን ቋንቋ ለምን አላማ ብሎ ይማረዋል? በቋንቋው በወቅታዊ ጉዳይ ወይስ ለዘለቄታው ለመጠቀም ይሻላል? ትምህርቱ የቀረበበት ሁኔታ ምንድነው? ለቋንቋውና ለትምህርቱ ያለው ፍላጎትና አመለካከት ምን ይመስላል? ተማሪው የወጣበት ቤተሰብ፣ ህብረተሰብ፣የትምህርት ተቋምና መንግስት ከትምህርት መጨረሻ ምን እንደሚደረግለት ይጠብቃል፣ ተማሪው ምን አይነት ባህርይ እና የቋንቋ ክሂል እድገት እንዲመጣ ይፈልጋል ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎች ለመረጃ አሰሳ ምንጮችና በትምህርት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮች በመሆናቸው በመጀመሪያ አሰሳ ሊደረግባቸው ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ Dubin (1986) አገላለፅ የመማሪያ መጽሐፍ በተማሪው ማንነት ላይ ተመስርተው በጥንቃቄ ከተዘጋጁ የተማሪው የመማር ፍላጎት አነቃቅተው ለቋንቋ እና ለትምህርቱ የሚቀርበውን አመለካከት አዎንታዊ አድርገው ለጥሩ ውጤት ያደርሳሉበማለት አብራርተዋል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ በተጨማሪ ሲያጠናክሩ መማሪያ መጽሐፍ ተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ለትምህርቱ ያላቸዉን ፍላጎት ለማበረታታት የሚከተሉትን ጭብጦች ይይዛሉ በማለት ያብራራሉ፡፡

እነሱም በመጽሐፉ አማካይነት ለተማሪዉ እንዲቀርቡ የተፈለጉት የትምህርት ልምምዶች የማስተማሪያ መሪሆች፣ የትምህርት ይዘቶችና ስልቶች ከመረሀ ትምህርቱ ጋር የተጣጣሙ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የመማሪያ መጽሐፍት መምህሩ እንዲያስተምር፣ ተማሪዉ እንዲማር የሚረዱ ሆነዉ የተዘጋጀ እንጂ ጫና የሚፈጥርባቸው መሆን የለባቸውም፤ የመማሪያ መጽሐፍት አራቱን የቋንቋ ክሂላት አዋህዶ እንዲይዙ ሁነው የተዘጋጁ እንጂ ለአንዱ ክሂል ትኩረት ሰጥተዉ ሌላውን ዘንግተዉ መዘጋጀት የለባቸውም፤ የመማሪያ መጽሐፍት በመምህሩም ሆነ በተማሪው ሊተገበሩ የሚችሉ የትምህርት ይዘቶችና ልምዶችን መያዝ

አለባቸው። አጥኝዋ ከላይ የተዘረዘሩትን የምሁራን ሀሳብ ስትረዳ የመማሪያ መጽሐፍት ሲዘጋጁ ትኩረትና ጥንቃቄ ተሰጥቶባቸው ሊዘጋጁ እንደሚገባቸውነው።

## 2.7. አመለካከት ከውጤት ጋር ያለው ዝምድና

Mclauglin (1991፡126) እንደገለፁት ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ባህል ጥሩ አመለካከት ካላቸው በውጤታቸው አመርቂ የሆነ ውጤት ያስመዘግባሉ። እነዚህ ተማሪዎች በቋንቋው ሀሳባቸውን ነፃ በሆነ መንገድ ለመግለጽና ለተለያዩ ጉዳዮች በተለያዩ ቦታዎች ላይ ለብዙ ጊዜ በውዴታ ልምምድ የሚያደርጉ ናቸው። በመሆኑም ከቋንቋው ማህበረሰብ ጋር መስተጋብር የመፍጠር ፍላጎታቸውም ጠንካራ ይሆናል በማለት ይናገራል።

በቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪው የሚገጥመውንና በውስጡ የሚያልፍበት ሁኔታ፣ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት፣የቋንቋው መምህር፣ ማስተማርያ መሳሪዎች፣ አጠቃላይ የትምህርት ስርዓትና ሌሎች ማህበራዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር ተማሪዉ በሚያደርገዉ መስተጋብርና እንቅስቃሴ የሚመነጭ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከትን ያዳብራል። የዳበረዉ አመለካከት ደግሞ ተማሪው በትምህርት ሂደት ከሚያደርገዉ የመማር ጥረትና ከሚደርስበት ውጤት ጋር ይገኛል (ተዋበች 2003፣27) በማለት ገልጸዋል።

Gardner (1985፡41) ይህንን ጉዳይ አስመልክተው ተማሪዎች ለቋንቋው ባላቸው መጥፎ አመለካከትና ከማስተማርያ መሳሪዎች ዝግጅት ጥራት መጓደል የተነሳ ትምህርቱን ሊያጠኑና በወጉ ሊከታተሉ ስለማይፈቅዱ የፈተና ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል። ስለዚህ መምህሩ ለተማሪዎችና ለሚያስተምረው ቋንቋ በተጨማሪም ለሙያው ያለው አመለካከት በተማሪዎች ውጤት ላይ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ተገንዝበው ማስተማር አለበት ይላሉ።

አጥኚዋ ከተጠቀሰው ሀሳብ መረዳት እንደቻለችዉ አንድ የቋንቋ መምህር ለሚያስተምረው ትምህርት የማስተማርያ መሳርያ በቂ ዝግጅት ከሌለው በተማሪዎች ዉጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ነው፡፡

Mclauglin (1991፡32) ገለፃ ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ መልካም አመለካከት ካላቸው በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ ከመሆናቸውም በላይ በራሳቸው ላይ የተደላደለ መተማመን ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ በራሳቸዉ የሚተማመኑ ተማሪዎች ደግሞ የቋንቋውንም ትምህርት በፍላጎትና ባላሰለሰ ጥረት ስለሚማሩ ውጤታቸው የተሻለይሆናል ይላሉ፡፡

በትምህርት ቤት በርካታ ተማሪዎች በግጭት ሰበብ ሲጎዱና ግጭቱን ችለው የሚማሩ አልያም የግጭቱ ተሳታፊ በመሆን በትምህርት ውጤታቸውና በአመለካከታቸው ላይ ትልቅ ተፅእኖ ይፈጥራሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ መልካም ስነምግባርና አዎንታዊ አመለካከት የተላበሱ ተማሪዎች እኩያቸውን ውጤታማ እንዲሆኑ በመርዳትና በቋንቋም ሆነ በሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች በመማር ማስተማር ላይ ችግሮችን በመቅረፍ የመማር ማስተማሩን ሂደት ያመቻችላቸዋል በማለት (Hurolck, 1996:26) ገልፀዋል፡፡

Ellis (2008) "የተማሪ አመለካከት በተማሪው የሁለተኛ ቋንቋ ውጤት ላይ ተፅእኖ እንዳለው ያምናል" (ገጽ 287)፡፡ ተማሪዎች በመማር ሁኔታ ላይ ያላቸው አመለካከት በተነሳሽነታቸውና በውጤታቸው በስኬቶቻቸውም ላይ ትልቅ ተጽእኖ እንዳለው Tremblay እና Gardner የገለፁትን የቅርብ ጊዜውን የጋርደን ማህበራዊና ትምህርታዊ ሞዴልን ያብራሩት Masgoret and Gardner (2003) ማረጋገጣቸውን ገልፀዋል፡፡ ቋንቋን በመማር ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ብዙ ምክንያቶች እንዳሉ ጥናቶች አመላክተዋል፡፡ ከነዚህም ምክንቶች መካከል ዕድሜ ፣ተነሳሽነት፣አመለካከት ፣የመማር ማስተማር ስልት፣ የግል ስብዕና፣ የትምህርት ግብዓቶች ፣ ቤተሰብ ፣ጓደኛና አካባቢ የመሳሰሉት ቋንቋን በመማር ላይ ተፅእኖ ከሚያሳድሩት ምክንያቶች

ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ምሁራን ይስማማሉ፡፡ማስጎሬት እና ጋረድነር (2003) ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር አመለካከትና ተነሳሽነት በጣም አስፈላጊና መሰረታዊ ናቸው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ምክንያቱም አብዛኞቹ ሁለተኛ ቋንቋን መማር ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶች በአመለካከትና ተነሳሽነት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው ነው በማለት ምሁራኑ አክለው አብራርተዋል፡፡

ሁለተኛ ቋንቋን ከመማሩ አንፃር አመለካከት የተነሳሽነትን እንደሚወስን የሚያረጋገጡ ብዙ መረጃዎች አንዳሉ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ብዙ ምሁራን የዚህን የአመለካከትና ተነሳሽነት የርስ በርስ ግንኙነት እውቅና ሰተዋል(ጋርደር፣1985 ፣2005 ፣ክርው፣1994 ዶርነይ፣1998 ማላላህ2004፣)፡፡

ዮሴፍ (2012) ሁለተኛ ቋንቋን መማር ውስብስብ የሆነ ሂደት መሆኑንና የተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ተጽእኖ የሚሳድሩበት መሆኑን በመግለጽ ከነዚህ ተፅእኖዎች መካከል አመለካከት ሁለተኛ ቋንቋን መማር ላይ ዋነኛ ተፅእኖ እንደሚያሳድር አሳውቋል፡፡

ዶርነይ (2006) ሁለተኛ ቋንቋ በተሳካ ሁኔታ ለመማር ብዙ ሁኔታዎች የሚያስፈልጉ ቢሆንም ብዙዎቹ መ/ራንና ተመራማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን በውጤታማነት ለመማር አመለካከትና ተነሳሽነት ቁልፍ ምክንያቶች እንደሆኑ ይስማማሉ፡፡ እንደ Wu (2010) ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት እንዲጨምርና ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ አመለካከት ዋነኘ ምክንያት እንደሆነ አብራርቷል፡፡

በካናዳ ዉስጥ ተማሪዎች ለፈረንሳይ ካናዳዊያን ማህበረሰብ ያላቸዉን አመለካከት ከማነቃቃት ጋር በማያያዝሰፊ ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡ ታደለ (1990፣139) የነዚህ ሙሁራን የጥናት ውጤት ተማሪዎች ለቋንቋው፣ ለትምህርቱና ለተናጋሪዉ ማህበረሰብ ያላቸዉን አመለካከትና መነቃቃት ለቋንቋውና ለትምህርቱ ሂደት መፋጠን ቁልፍ ጉዳዮች መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

Harmer (1990) ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት ለተናጋሪው ማህበረሰብ ያላቸው አመለካከት ፋይዳ ያለዉና የተለየ ሚና የሚጫወት ሳይሆን ወሳኙ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ህፃን ወደ ማያውቀው ቦታ ሲወሰድ ከሚያገኛቸው ህጻናት ጋር መግባባት አይችልም፡፡ ይሁን እንጂ ከብቸኝነት ለማምለጥ ሲል ለቋንቋውና ለቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ያለው አመለካከት ምንም ይሁን ምን በፍላጎት ተነሳስቶ ቋንቋውን ይማረዋል ይላሉ፡፡

ይህንን ሀሳብ Gardner (1985፡41) ሲቃወሙ ፍላጎት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያደርስ ተናግረዋል፡፡ ስለዚህ ለቋንቋውና ለትምህርቱ በጎ አመለካከት ከሌለ ፍላጎት አይመነጭም፡፡ እንግሊዘኛን አይርሽኛ እንዲተካው መደረጉ በአይርሾች ፍላጎት ወይም በሁኔታዎች አስገዳጅነት ለመሆኑ መሰረት ያለው ጭብጥ አልቀረበም፡፡

Gardner & Lambert (1972,1985) ሁለተኛ ቋንቋን የመማር አመለካከትና በሁለተኛ ቋንቋ ውጤት መካከል ስላለው ዝምድና ባጠኑት ጥናት እንደተገለፀው በአመለካከትና በውጤት መካከል አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን ከዚህ የጥናት ውጤት በተቃራኒ Lanara (1999) ,በአመለካከትና ውጤት መሀከል ምንም ግንኙነት እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

Karaş (1997), ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ባላቸው አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መሀከል አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩን በማመላከት ግንኙነቱ ጠንካራ አለመሆኑን አብራርተዋል፡፡

በመሆኑም አመለካከት በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ ያለዉ ተፅዕኖ እንደ አንድ ወሳኝ ተላዉጦ መታየት አለበት የሚል አቋማቸውን ያሰምሩበታል፡፡ ስለዚህ ከምሁራኑ የጥናት ውጤትና አገላለጽ አጥኝዋ እንደተረዳችው አመለካከት ከተማሪዎች ትምህርት እንቅስቃሴና ውጤት ጋር የቅርብ ግንኙነትና ተዛምዶ ያለው ትምህርታዊና ማህበራዊ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

ሁለተኛ ቋንቋ መማር ላይ ፆታ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድር እና አንዱ ጾታ ከሌላው የበለጠ ስኬታማ ስለመሆኑ ላይ የሚጋጩ ጥናቶች እንዳሉ ገልፀዋል (Ellis, 1994)፡፡ ከዚህ አንፃር ብዙ ጥናቶች የተሰሩ ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋን መማር ከፆታ አንፃር ልዩነት ስለመኖሩ ተመራማሪዎች ያላቸው አመለካከት የተለያየ ናቸው፡፡ Bacon (1992) (Akram & Ghani, 2013) ሁለተኛ ቋንቋ ከመማር አኳያ በጾታ መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ ያብራሩ ሲሆን Gardner and Lambert (1972) Spolsky (1989) ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ሴት ተማሪዎች ከወንዶች የበለጠ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው አመላክተዋል፡፡

Ludwig (1983) ወንድ ተማሪዎች ከሴቶች የተሸለ አዎንታዊ አመለካከት እንዳለቸው ሲያብራሩ Abu-Rabia(1997) ወንድ እና ሴት ተማሪዎች በካናዳ ውስጥ እንግሊዝኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ተመሳሳይ አዎንታዊ አመለካከትና ተነሳሽነት እንዳሳዩ አብራርተዋል፡፡

በአጠቃላይ ሁለተኛ ቋንቋ መማርከፆታ እንጻር ልዩነት ያለው ስለመሆኑ ከተለያዩ ጥናቶች የተገኙ ውጤቶች ወጥነት የሌላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

## 2.8. የቀደምት ጥናት ቅኝት

በዚህ ጥናት ስር ከሚነሱት ጉዳዮች መካከል አንዱ ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ቅኝት ነው፡፡ የጥናቱ አቀራረብም የሁለተኛ ዲግሪ የቀረቡ የትኩረት ነጥቦች፣ ውጤቶችና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ባጭር ባጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

እሸቱ (1997) ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸው ፍላጎትና በውጤታቸው መካከል ያለግንኙነት (በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን) የሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጹሐፍ ነዉ፡፡ መረጃ መሰብሰቢያ የጹሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች፣ የሰነድ ፍተሻ በማድረግ ሰብስበዋል፡፡ በተማሪዎች ፍላጎትና ውጤት መካከል አዎንታዊ ግንኙነት እንዳለ ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡ አማርኛ ቋንቋ ለመማር ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ሲያስመዘግቡ፤ ዝቅተኛ

ፍላጎት ያላቸው ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸዉ ፍላጎትና ውጤት መካከል የጎላ ልዩነትእንዳለ አረጋግጠዋል፡፡ በተጨማሪ ከቦታና ከትምህርትቤት አንፃር የተማሪዎች ፍላጎትና ውጤት እንደሚለያይ አረጋግጠዋል፡፡

አበበ (2003) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ጥናት ትኩረት የአዲስ አበባ የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በዉጤታቸዉ መካከል ያለው ዝምድና በሚል አቅርበዋል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያቸዉም ለተማሪዎች የጹሁፍ መጠይቅ፣ ለመምህራን ቃለመጠይቅ እና የክፍል ውስጥ ምልከታ በማድረግ መረጃ ሰብሰበዋ፡፡ በጥናቱ የተመዘገበዉ ዉጤት እንደሚያመለክተው ተማሪዎቹ ለመምህሩ፣ ለመማሪያ መጽሀፋቸው እና ለፈተና ውጤታቸው አዎንታዊ አመለካከት አስመዝግበዋል፡፡ እንደዚሁም ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡

ፀጋዬ (1996) ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረበ ማሟያ ጹሁፍ ሲሆን የጥናታቸዉ ርዕስም ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸዉ አመለካከት ላይ ዝምድና ያላቸው ተላዉጦዎች፤ በአዱስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስታዊ ባሌሆኑ ትምህርት ቤቶች የሚል ነው፡፡

በጥናቱ ላይ የተተኮረባቸው አበይት ነጥቦች ተማሪዎች ለታለመው ቋንቋ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆንን አስመልክቶ መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አዎንታዊነትና አሉታዊነት ውሳንኤዎች ምንድን ናቸው የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነው፡፡ የተጠቀሙባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በወላጆች፣ ለተማሪዎችና በመምህራን የሚሞሉ የፅሁፍ መጠይቆች በማሰራጨት የቃልመጠይቅና የክፍል ምልከታ በማካሄድ ከተጠኝዎቹ የተረጋገጠ መረጃ አግኝተዋል፡፡

በጥናታቸውም ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋንና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለይተዉ በመገንዘብ አማርኛ ቋንቋ በመሆኑ እንወዳለን ሲሉ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ግን በአብዛኛው አዎንታዊ አለመሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ አልፎ አልፎ ግን ለቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ተገኝተዋል ብለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ተመሳሳይነት ለአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚኖራቸው አመከካከት የሚያጠና በመሆኑ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ አመለካከትን የሚለውጡትን ተላውጦዎች መዳሰሱና መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች ላይ ማተኮሩ ነው፡፡

ተዋበች (2003) ጥናቱም ትኩረት ያደረገው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከፍኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸዉ አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና የሚል ነዉ፡፡ ጥናቱ ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋና ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው አረጋግጠዋል፡፡ ተማሪዎች ለቋንቋ መምህራን ያላቸዉ አመለካከት በከፍተኛ ደረጃ አሉታዊ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል፡፡ መማርያ መጽሀፍ በተማሪዎች ቋንቋ ትምህርት ላይ ዝቅተኛ አመለካከት እንዲኖራቸው በር ከፋች እንደሆነ የተሰጠዉ ውጤት ጠቁሟል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ወላጆች ምክንያት መሆናቸውን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ መረጃውን ለመሰብሰብ የተጠቀመችው መሳሪያ የጽሁፍ መጠይቅ፣ የቃለመጠይቅ፣ የክፍል ምልከታና ሰነድ ፍተሻ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ የዚህ ጥናት ተመሳሳይነት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ያላቸውን አመለካከት ማጥናቱ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ አመለካከትን የሚለውጡ ተላውጦችን መዳሰሱና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ከፍኛ መሆኑ ነው፡፡

ታሪኩ (1988) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ  የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን ጥናቱ መሰረት ያደረገው‹‹የአዲስ አበባ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አመለካከቶች በመረጃ ማረጋገጥ

አሉታዊ የሆኑ ጉዳዮች ወደ አዎንታዊነት የሚቀየሩበትን አዎንታዊ የሆኑትን ጉዳዮች ደግሞ ይበልጥ የሚጠናከሩበትን መንገድ መጠቆም ሲሆን የዚህን ዉጤት ለማወቅ ለተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ ለመምህራን ደግሞ ቃለመጠይቅ ተጠቅሟል፡፡ የናሙና አወሳሰድም ትምህርትቤቶችን በዕጣ ናሙና፣ ተማሪዎችን በነሲብ ናሙና ሲሆን መምህራንን ደግሞ ሙሉ በሙሉ አካቷል፡፡ ይህ ጥናት በአይነታዊና በመጠናዊ ዘዴ በመተንተን ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን አይንቁም፣ አይጠሉም፣ መማር ይፈልጋሉ፡፡ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በስፋት ይጠቀማሉ፡፡ ሲያነቡና ሲያዳምጡ ከሌሎች ቋንቋዎች ይልቅ አማርኛ ሲሆን ይገባቸዋል፡፡ ተማሪዎች አማርኛ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቋንቋ እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸውን ዝንባሌ ይደግፋሉ፡፡ በተጨማሪም ልጆቻቸው አማርኛን በቤት ውስጥ ቢናገሩበትና ከፍተኛ ትምህርት ቢገፉበት አይቃወሙም፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጥሩ ፀባይና በቂ ዕውቀት ያላቸው ሲሆን ቋንቋውን በደንብ ያስተምራሉ፡፡ ተማሪዎቻቸውም አማርኛን እንዲወዱና በፍላጎታቸው መሰረት እንዲማሩ ይመክራሉ፡፡ መጽሀፍ የቋንቋ ዘርፎችን እኩል አመጣጥኖ ስላልያዘ ያለአስተማሪ ተማሪን መምራት ስለማይቻል ብቃት ይጎለዋል፡፡ ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት በማንሳቱ ሲሆን የሚለየው ደግሞ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚወስዱ ተማሪዎችን ለይቶ ባለማጥናቱ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ጉዳዮች በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ማጥናቱ ይለየዋል፡፡

ወንደሰን (1989) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ የቀረበ ጥናት ሲሆን ትኩረት ያደረገዉ ‹‹የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆኑ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለው ዝምድና›› በሚል ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ ለተማሪዎችና ለመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የናሙና አወሳሰድም የተማሪዎች ከቁጥራቸው አንጻር

በብድግ ብድግ ናሙና አወሳሰድ ዘዴ ሲሆን መምህራን ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተወስደዋል፡፡ ምልከታን በደጋፊነት ተጠቅመዋል፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት ተማሪዎች ለመምህራን ዝቅተኛ አዎንታዊ አመለካከት ያሳዩ መሆኑን፤ ለ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍት አሉታዊ አመለካከት ያላቸው መሆን፤ የተማሪዎች ወላጆችና ህብረተሰቡ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት እንዲቀርጹ አጋዥ መሆናቸው፤ አጠቃላይ የአመለካከት ድምር አማካይ ውጤት ለአማርኛ ቋንቋና ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አዎንታዊ አመለካከት አሳይተዋል፡፡ በተማሪዎች አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከል ፋይዳ ያለው  ተዛምዶ መኖሩን ስሌቱ እንዳሳየ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ማለት ዝቅተኛ አዎንታዊ አመለካከት ከዝቅተኛ የማለፊያ ውጤት ጋር ዝምድና እንዳለው አሀዞቹ እንደሚያሳዩ ተጠቅሷል፡፡ መምህራን ለተማሪዎች፣ ለመማሪያ መጻህፍትና ለመምህርነት ሙያቸው ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አጥኝው ከላይ ከተጠቀሱት ውጤቶችን በማንሳት ለተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት ዝቅተኛ መሆን የመምህራን የአመለካከት ውጤትና የትምህርት የክፍል አያያዥ ብቃት አነስተኛ መሆን ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነጥብ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት የሚመረምር ሲሆን ፤የሚለየው ደግሞ ተተኳሪ በሆኑ ተማሪዎች፣ ፖልቲካዊና ባህላዊ ጉዳዮች በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በማንሳቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡ አጥኝዋ ባደረገችው ዳሰሳም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ማለትም የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና ውጤት ተዛምዶ የሚል ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች አለማጋጠሙ አጥኚዋ ይህን ርዕሰ ጉዳይ ለማጥናት  ተነሳስትለች፡፡ ይህ ጥናት ከእሸቱ ከአበበና ከተዋበች የሚለየው ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ የአመለካከትና የአማርኛ ፈተና ውጤት የዝምድና መጠንን በጥልቀት መመርመሩና የዝምድና መጠኑ መካከለኛ መሆኑን በማረጋገጡ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን ይከተላል።በመሆኑም ለጥናቱ የሚሰበሰቡት መረጃዎች አይነታዊና መጠናዊ በሆነ መንገድ ተተንትነው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳመኛ የሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ውጤት በገለፃ መልክ ቀርቧል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

በሲዳማ ክልላዊ መንግስት በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ ስር መንግስታዊ የሆኑ ዘጠኝ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ መረጃውን በቅርብ ማግኘት የሚቻልበት አንድ ትምህርት ቤት በዓላማዊ የናሙና አወሳሰድ ተመርጧል፡፡

ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት አጥኝዋ ቀደም ሲል ስለተጠኝዎቹ ማንነት ባላት ዕዉቀት መሰረት ለሚነሳው ጥያቄ ምላሽ ይሰጡኛል ብላ በማሰብ የመረጠችው ናሙና ነው፡፡ በተጨማሪ ይህ ትምህርት ቤት በከተማው ከሚገኙት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 50% ሲዳምኛ አፊ ፊት የሚሆኑ ተማሪዎችን የያዘ በመሆኑና ለስራዉ ብቃት ያለው መረጃ የሚገኝ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ግንዛቤ መሰረት ተገቢነት ያለው መረጃ ለማግኘት አመቺ ሆኖ የተገኘው የምስራቅ ጮራ  የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርጧል፡፡

## 3.3 የጥናቱ ተሳታፊዎች

ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት በመጀመሪያ ተማሪዎችን የመለየት ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በአጠቃላይ አስረኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች ውስጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑት ብቻ ከትምህርት ቤቱ ተለይተዋል፡፡  ከነዚህ ከተለዩት ተማሪዎች መካከል

35% በስርዓት የተቀረፀ እኩል እድል ሰጪ ናሙና ዘዴ ከትምህርት ቤቱ ተጠኚ የሲዳምኛ አፊፊት የሆኑ ተማሪዎች ከምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ከተመዘገቡት295 ተማሪዎች ዉስጥ 103 ተማሪዎች ከላይ በተገለጸዉ አመራረጥ ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል፡፡ይህ ዘድ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎችን በስም ቅደም ተከተል በማስቀመጥ ለሚመረጥ ንሞና ተመራጭ በመሆኑ ነው

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

በጥናታዊ ምርምር ሂደት ለመረጃ መሰብሰቢያ በጥቅም ላይ የዋሉት የጹሁፍ መጠይቅና ሰነድ ፍተሻ ናቸው፡፡

### 3.4.1 የፅሁፍ መጠይቅ

ይህ ጥናት የታቀደውን ዓላማ ይመታ ዘንድ ከተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች አንዱ የፅሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህም ባለ አምስት የደረጃ ድልድል መለኪያ መስፈርት /Likert scale/ አፃፃፍ ስልት የተዘጋጁ መጠይቆች ለተማሪዎች ቀርቧል፡፡መጠይቆቹ ሲዘጋጁ በውስጣቸው አዎንታዊና አሉታዊ መንፈስ ያላቸው ዝግ ጥያቄዎችን አካተው እንዲይዙተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

አመለካከትን የሚለካ መጠይቅ ለማዘጋጀት የተለያዩ ሊቃውንት ያዘጋጁትን የአመለካከት መለኪያ መጠይቆችን ለማየት ተሞክሯል፡፡ የዚህን ጥናት የፅሁፍ መጠይቅ ለማዘጋጀትም የBoonrangsri, K, Chuaymankhong, D, Remyindee, N, &Vongchittpinyo, N,(2004) and gardner(1985). የአመለካከት መለኪያ መጠይቆችን እና ፅንሰ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ የመጠይቁን ተቀባይነት ደረጃ ለማረጋገጥ በሁለት የትምህርት ባለሙያዎችና በጥናቱ አማካሪ በማስገምገም የተቀባይነት ደረጃውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የፅሁፍ መጠይቁን ውስጣዊ አስተማማኝነት/ internal consistency of the reliability/ በተመለከተ የክሮምባች /crombach Alpha/ የአስተማማኝ መለኪያ ዘዴን በመጠቀም

የመጠይቁን አስተማማኝ ደረጃን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በስሌቱም መሰረት የተገኘው ውጤት 0.815 ነው ፡፡ በመሆኑም የመጠይቁ አስተማማኝነት ተረጋግጧል፡፡ በመስክ ጥናት ጊዜ አስተማማኝነቱ ከታወቀ በኋላ ተማሪዎቹ መጠይቁን በመመሪያው መሰረት እንዲሞሉ ተደርጎ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

3.4.2 ሰነድ ፍተሻ

የጥናቱ ተሳታፊዎች በአንደኛ መንፈቅ ዓመት ያገኙት ውጤትና አመለካከት በተዛምዶ ቀመር ተሰልቶ በሁለቱ መካከል ያለው ጥምረት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ይህንን የጥምረት ዉጤት የበለጠለማጠናከር የተጠኝዎችን የአንድ የምዘና ወይም የፈተና ዉጤት ብቻ ወስዶ ከማስላት ይልቅ በዓመቱ አጋማሽ ዉጤት መመዘኑ የተሻለ ስለሚሆን የ2015ዓ.ም የአስረኛ ክፍል የአንደኛ መንፈቀ ዓመት የአማርኛ ፈተና ዉጤት ድምር ተወስዶ በቀመር ስሌት መሰረት ተተንትኖ የተገኘው ዉጤት ተተርጉሟል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከተማሪዎች የሚሰበሰቡት መረጃዎች ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን አንደኛው ስለተማሪ ማንነት፣ የብሄረሰቡን ሁኔታ የሚገልፁ ዳራዊ መረጃ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ተማሪው በአማርኛ ቋንቋና በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ የሚረዱ አመልካች ጥያቄዎች ያሉበት ክፍል ነው ፡፡የፅሁፉ መጠይቅ ተተኳሪ ተማሪዎችን በሚመጥን መልኩ ባለ አምስት የደረጃ ድልድል መለኪያ መስፈርትበሊከርት አፃፃፍ ስልት መለኪያዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ ሲሆን ከተማሪዎች የተገኙት ምላሾች በመጠናዊ ዘዴ ተሰልቶ በገለፃ መልክ በገላጭ ምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በሌላ በኩል በመጠየቁ ላይ በሰፈሩት ተራ ቁጥርናቅደም ተከተል መሰረትእንደየባህሪያቸው በአማካይ እየተሰሉና እየተተነተኑ በሰንጠረዥ ተቀናብረው ቀርበዋል፡፡በሰነድ ፍተሻም የጥናቱ አብይ ጉዳይ የሆነውን የተማሪዎች የአመለካከትና የውጤት ዝምድና ለመፈተሽ የአንደኛ መንፈቀዓመት የፈተና ዉጤት ድምር ተወስዷል፡፡ የአመለካከት

ዉጤት ከፈተናዎች የአማካይ ውጤት ጋር በየፒርሰን ተዛምዶ ቀመር ተሰልቶ እየተነጻጸረ ተተንትኗል፡፡

የመረጃት ንተና የፒርሰን ትስስርን /pearson correlation/ በመጠቀም ተከናውኗል ፡፡የፒርሰን ተዛምዶ በሁለት ተለዋዋጮች መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን የሚለካ ስታቲስቲክስ ነው፡፡ የፒርሰን ተዛምዶ ዘዴ ለተለዋዋጮች ቁጥር መጠቀም በጣም የተለመደው ዘዴ ነው; በ-1 እና 1 መካከል ያለውን ዋጋ ይመድባል፣ 0 ምንምተያያዥነትየለውም፣ 1 ጠቅላላ አወንታዊ ተዛምዶ ሲሆን - 1 አጠቃላይ አሉታዊ ተዛምዶ ነው፡፡ከ 0 በላይ ያለው ተዛምዶ እንደሚከተለው ይተረጎማል፡ ከ0.1--0.3 ዝቅተኛ ከ0.3--0.5 መካከለኛ ከ0.5 በላይ ከፍተኛ ተዛምዶ ይኖሩታልኮሄን ጄ /Cohen, J. (1988)/፡፡

## 3.6. ጥናቱ የተሰራበት ስነ-ምግባር፡

ይህጥናት ሰዎች የሚሳተፉበት በመሆኑ የሚከተሉት የምርምር ስነ ምግባሮች ለመረጃ አሰባሰብ ተግባር ታሳቢ ተደርገዋል/ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

1. ጥናቱከ መጀመሩ በፊት በአጥኚዋ የተጻፈ የፍቃድ ደብዳቤ ለተጠያቂ ትምህርት ቤት ኃላፊዎች ተልኳል፡፡
2. በጥናቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም ምላሽ ሰጪዎች ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት ስምምነታቸውን አሳውቀዋል፡፡
3. በዚህ ሥራ ውስጥ ትምህርት ቤቱ እና ምላሽ ሰጪዎች ስማቸውን መፃፍ ሳይጠበቅባቸው መረጃ እንዲሞሉ በማደረግ የግል ሚስጥራቸው እንዲጠበቅ ተደርጓል፡፡
4. ሁሉም የተሰበሰቡ መረጃዎች አጥኚዋ ብቻ በሚስጥር በያዘችው በይለፍ ቃል በተጠበቀ የግል ኮምፒውተር ላይ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡-የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1. የተጠኚዎች አጠቃላይ ዳራ

### 4.1.1.ፆታ

በናሙናነት የተወሰዱት ተማሪዎች በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከ10ኛ ክፍል በጠቅላላው 103 ተማሪዎች በናሙናት ተወስደዋል፡፡

**ሰንጠረዥ አንድ፡ የተማሪዎች የፆታ ስብጥር**

| ፆታ | ጠቅላላ ተማሪዎች | |
|---|---|---|
| | ብዛት | % |
| ወንድ | 50 | 48.5 |
| ሴት | 53 | 51.5 |
| ድምር | 103 | 100 |

## 4.2 የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋናዓላማ የተማሪዎች አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ነው፡፡ ከታለመው ውጤት ላይ ለመድረስ አጥኚዋከተጠቀመችበት የመረጃ መሰበሰሰቢያ መሣርያ አንዱና ዋነኛው የፅሑፍ መጠይቅ ማስሞላት ነው፡፡

በዚህ መሰረት 28 ጥያቄዎችን ያዘለ መጠይቅ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ 103 ተማሪዎች እንዲሞሉት ተደርጓል ፡፡መጠይቁ ሳይባክን ምላሹን ለማግኘት እንዲቻል እንዲሁም ስለአሞላሉና ግልፅ ላልሆኑ ሀሳቦች ማብራሪያ ለመስጠት እንዲያመች ከትምህርት ቤቱ የተመረጡት ተማሪዎች በሙሉ አጥኚዋ በአካል በተገኘችበት መጠይቁን ሞልተዋል፡፡

ጥናቱ  አመለካከትን ከውጤት ጋር አነጻጽሮ የሚመረምር በመሆኑ የተመረጡት ተማሪዎች በሚሞሉት መጠይቅላይ አጥኚዋ ብቻ የምታውቀው መለያ /ኮድ/ ተደርጎ ተሞልቷል፡፡ የመለያው ምክንያትየአንድን ተማሪ አመለካከት ከሌላው ተማሪ የፈተና ውጤት ጋር እንዳይቀላቀልለማድረግና መጠይቁን የሞሉ ተማሪዎችን የፈተና ውጤት ብቻ ከትምህርት ቤቱ በትክክልለማግኘት እንዲቻል የተደረገ ስሌት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከትምህርት ቤቱ ጥናቱ የሚመለከታቸው ተማሪዎች ውጤት በአማርኛ መምህር ፊርማና በትምህርት ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ከማርክ ሊስት ተለቅሟል፡፡

መጠይቁ ከተሞላበኋላእያንዳንዱ ተማሪ ያስመዘገበውን የአመለካከት ውጤት ወደ በSPSS ሶፍትዌር ፕሮግራም በማስገባት ተተንትኗል፡፡የመጠይቁን አስተማማኝነት የአመለካከትና ውጤት ዝምድና ማረጋገጫ ስታቲስቲካዊ ስሌት ተደርጎበታል፡፡የተገኘው የተማሪዎች ውጤት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ ሁለት፡ የአመለካከት አማካይ ልኬት መግለጫ**

| ልኬት | የአማካይ ወሰን | የአመለካከት ደረጃዎች | የውጤት ወሰን |
|---|---|---|---|
| 1 | በጣም አልስማማም | ከፍተኛ አሉታዊ | 1–1.99 |
| 2 | አልስማማም | አሉታዊ | 2–2.99 |
| 3 | ለመወሰን እቸገራለሁ | ገለልተኛ | 3.00 |
| 4 | እስማማለሁ | አዎንታዊ | 3.00–3.99 |
| 5 | በጣም እስማማለሁ | ከፍተኛ አዎንታዊ | 4.00–4.99 |

ከላይ በሰንጠረዡ የተገለፀው ለእያንዳንዱ የተማሪው አመለካከት አማካኝ ነጥብ ያለውን ስሌት የሚያሳይ ነው ፡፡ከፍተኛ ነጥብ ማለት ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸውና ዝቅተኛ ነጥብ ደግሞ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ መማር ላይ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ከ(ኪትጃሮንይ፣2013፣ገጽ26) የተወሰደ

## 4.2.1 ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋናትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ትንተና

በዚህ ተላውጦ ስር ተማሪው ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያለውን አመለካከት ለማወቅ 16 አዎንታዊና 12 አለታዊ ስሜትን የሚያንፀባርቁ በድምሩ ሃያ ስምንት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ የተሰጠውምላሽ በሠንጠረዥና በገለጻ ቀርቧል፡፡

### ሠንጠረዥ-ሶስት፡ተማሪዎች በአጠቃላይ ያስመዘገቡት የአመለካከት ውጤት

| የመጠይቆች ብዛት | ለምላሾች የሚሰጥ የብዜት ዋጋና የተማሪዎች ብዛት | | | | | የአመለካከት ድምር ውጤት | አጠቃላይድምርውጤት /total frequency | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 | | | |
| | ምን ያክል ጊዜ ተመረጠ | ምን ያክል ጊዜ ተመረጠ | ምን ያክል ጊዜ ተመረጠ | ምን ያክል ጊዜ ተመረጠ | ምን ያክል ጊዜ ተመረጠ | | | |
| 28 | 462 | 581 | 335 | 802 | 704 | 2884 | 7947 | 2.755 |

ከዚህ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው103 ተማሪዎች ከ28 ጥያቄዎች በጣም እስማማለሁ 462 ጊዜ፣ እስማማለሁ 581 ጊዜ ፣ ለመወሰን እቸገራለሁ 335 ጊዜ፣ አልስማማም 802 ጊዜ እና ፈጽሞ አልስማማም 704 ጊዜ የተመረጡ ሲሆን የነዚህ ምላሾች ድምር 462 +581 +335 802 +704 = 2884 (የአመለካከት ድምር ውጤትን) አስገኝቷል ፡፡እነዚህ ምላሾች ለምላሹ በተሰጠው ዋጋ ተባዝቶ (462 *5 + 581 *4 + 335 * 3 + 802 * 2 + 704 *1 = 7947 (የአጠቃላይ ድግግሞሽ ድምር) ሆኗል ፡፡ ይህን የአጠቃላይ ድግግሞሽ ድምር ለአመለካከት ድምር በማካፈል( 7947/2884 = 2.7555 (የአመለካከት አማካይ ውጤት) ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም በሃያ ስምንቱ ጥያቄዎች ላይ መቶ ሶስቱ ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት 2.755 በመሆኑ ተማሪዎችለአማርኛ ቋንቋና ትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ከሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ-አራት፡ተማሪዎችያስመዘገቡት ከፍተኛና ዝቅተኛ የአመለካከት ውጤት

| | የተማሪ ቁጥር | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|
| አመለካከት | 103 | 1.93 | 3.64 | 2.755 | .39 |
| የተማሪ ቁጥር | 103 | | | | |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተገለፀውለተላውጦ (ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት) ተማሪዎች ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከት 1.93 ሲሆን ከፍተኛ የአመለካከት ውጤት 3.64 መሆኑ ታይቷል ።

### 4.2.2. የተማሪዎች አመለካከት በፆታ

ከላይ እንደተገለፀው የተማሪዎች የተጠቃለለ የአመለካከት አማካይ ውጤት አሉታዊ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በመቀጠል ከዚህ አጠቃላይ የተማሪዎች የአመለካከት አማካይ ውጤት ውስጥ አመለካከት በፆታ ልዩነት ያለው እንደሆነ መፈተሽ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ የታቀፉት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸውን አመለካከት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለመመልከት ተሞክሯል፡፡ ስለሆነም ውጤቱ ከመተንተኑ በፊት ለትንተናው ያመች ዘንድ የሚከተለውን ሰንጠረዥ እንመልከት

ሠንጠረዥ-አምስት፡ ተማሪዎች ያስመዘገቡት የአመለካከት ውጤትበፆታ

| ፆታ | የተማሪ ቁጥር | አማካይ ውጤት | ማዕከላዊ ልይይት | % |
|---|---|---|---|---|
| ሴት | 53 | 2.8080 | .36618 | 51.5 |
| ወንድ | 50 | 2.7000 | .41550 | 48.5 |
| ድምር | 103 | 2.7555 | .39272 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዡ የተመለከተው መረጃ እንደሚያሳየው መጠይቁን የሞሉ የወንድና የሴት ተማሪዎች ብዛትና በሀያ ስምንቱ ጥያቄዎች ላይ ያስመዘገቡትን አጠቃላይ የአመለካከት አማካይ ውጤት ነው፡፡በጥናቱ 50 (48.5) ወንዶችና 53 (51.5) ሴት ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን የተገኘው የአመለካከት አማካይ ውጤት ተለይቶ ተመዝግቧል፡፡ የወንድና ሴት ቁጥር የተለያየው በአጋጣሚ ከተመረጡት ኒሞና ስም ዝርዝር መቅደም ተከተል ሲፃፍ የተገኘ ቁጥር ነው ፡፡ በመሆኑም ወንዶች ተማሪዎች እና የሴቶች ተማሪዎች የአመለካከት አማካይ ውጤት ተቀራራቢነት ያለውና አሉታዊ መሆኑ ተለይቷል፡፡

## 4.2.3. አካዳሚያዊ ውጤት ትንተና

ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያስመዘገቡትጥቅልና ዝርዝር ውጤቶች በሚከተለው ሁኔታ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ አማካይ፣ማዕከላዊ ልይይት ፣ከፍተኛና ዝቅተኛ ጠቅለል ባለ ሁኔታና ዝርዝር ውጤታቸው ደግሞ ተናጠላዊ ብቃታቸው በሚታይበት መልኩ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ-ስድስት፡ተማሪዎች በአጠቃላይ ያስመዘገቡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት**

| | የተማሪ ቁጥር | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | አማካይ | ማዕከላዊ ልይይት |
|---|---|---|---|---|---|
| የግማሽ ዓመት ውጤት | 103 | 34 | 87 | 53.52 | . 10.513 |
| የተማሪ ቁጥር | 103 | | | | |

ከላይ በርዕሱ እንደተመለከተው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመዘገበው ዝቅተኛ ውጤት 34 ሲሆን ከፍተኛ ውጤት 87 መሆኑን ያሳያል፡፡የተማሪዎችን አጠቃላይ አማካይ ውጤት (53.52) ስንመለከት ውጤቱ ከ50% በላይ ቢሆንም ዝቅተኛ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ይህም የሚያመለክተው የተማሪዎች ውጤት ከፍተኛ አለመሆኑን ነው ፡፡

## 4.2.4.የተማሪዎች ውጤት በፆታ

ከላይ እንደተገለፀው የተማሪዎች የተጠቃለለ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤት ከ50% በላይ ቢሆንም (53.52) ዝቅተኛ መሆኑ ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ውጤት ከፆታ አንፃር የሚኖረውን ልዩነት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውየውጤት ልዩነት እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርቧል ፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት፡ተማሪዎች ያስመዘገቡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት በፆታ

| ፆታ | የተማሪ ቁጥር | አማካይ ውጤት | ማዕከላዊ ልይይት |
|---|---|---|---|
| ስት | 53 | 54.62 | 11.941 |
| ወንድ | 50 | 52.36 | 8.722 |
| ድምር | 103 | 53.52 | 10.513 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በጥናቱ የተሳተፉ 50 ወንዶችና 53 ሴት ተማሪዎች የግማሽ ዓመት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤት ተለይቶ ቀርቧል። ከሰንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከወንዶች ተማሪዎች ጋር ተቀራራቢ ቢሆንም የሴቶች ተማሪዎች አማካይ ውጤት ጥቂት ልዩነት ያሳየ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

## 4.2.5.**በአመለካከትና የፈተና ውጤትመካከል ያለው ተዛምዶ**

የጥናቱ ዋና ዓላማ የተማሪዎች አመለካከትና የፈተና ዉጤት ዝምድና አለው ወይስ የለውም የሚለውን ለማረጋገጥ ሲሆን እዚህ ዉጤት ላይ ለማድረስ የፒርሰን የተዛምዶ ቀመር አገልግልት ላይ ውሏል።

እንደ መለኪያ በቀረቡ የተላውጦ ጥያቄዎች ውስጥ ተማሪዎች አሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው የተጠናከረው መረጃ ያስረዳል። ተማሪዎች ለቋንቋ ያላቸው አመለካከት በትምህርት ቤቱ አብዛኛውን ተማሪ የአመለካከት ውጤት ስንመለከት አሉታዊ አመለካከት ሆኖ

ታይቷል፡፡ተማሪዎች ለቋንቋው ያላቸውን አመለካከት ከፈተና ውጤታቸው ጋር በንጽጽር ሲታይ ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በተዛምዶ ስሌት ቀመር/correlation/ ዉስጥ በማስገባት የፈተና ውጤት ከአጠቃላይ የተማሪዎች አመለካከት ጋር በማዛመድ 0.456ውጤት ለማግኘት ተችሏል፡፡ የተተነተነው የፈተና ውጤት የተማሪዎች የአንደኛ ወሰነ ትምህርት የአማርኛ ፈተና ውጤትሲሆን የአመለካከትደግሞ 103 ተማሪዎች በ28 ጥያቄዎች በተናጠል ያስመዘገቡት አማካይ ነጥቦች ተወስደዋል፡፡

**ሠንጠረዥ ስምንት ፡ የአመለካከትና የፈተና ውጤት ተዛምዶ በፒርሰን ተዛምዶ ቀመር**

| | ውጤት አመለካከት | ውጤት አመለካከት |
|---|---|---|
| ውጤት(ፒርሰን ተዛምዶ) | 1 | .456** |
| የጉልህነት ደረጃ | | .000 |
| የተማሪ ቁጥር | 103 | 103 |
| አመለካከት(ፒርሰን ተዛምድ) | .456** | 1 |
| የጉሌህነት ደረጃ | .000 | |
| የተማሪ ቁጥር | 103 | 103 |

ከላይ በሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎች አጠቃላይ አመለካካት አማካይና የአንደኛወሰነ ትምህርት በክፍል መምህራን የተሰጡ ፈተናዎች አማካይ ውጤት ያለው ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ ስሌት ቀመር መሰረት ተሰርቶ የተገኘው ውጤት (0.456)ነው ፡፡ ይህ ውጤት ከ0--1 ባለው መካከል የሚገኝ በመሆኑ ዎንታዊ ዝምድና መኖሩን አመላክቷል፡፡አዎንታዊ ተዛምዶአንደኛው ተለዋዋጭ ሲጨምር ሁለተኛ ተለዋዋጭ እየጨመረ

መሄዱንወይንም አንደኛ ተለዋዋጭ ሲቀንስ ሁለተኛው ተለዋዋጭ እየቀነሰ መሄዱን የሚያመለክት ተዛምዶ ነው። እንደ ኮሄን ጄ /Cohen, J. (1988)/ የተዛምዶ ልኬት መሰረት የተገኘው ውጤት(ከ0.3--0.5) መሀከልስለመጣ መካከለኛ ዝምድናን አሳይቷል። የዚህ ተዛምዶ ውጤትእንዳሳየውተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው መለካከትና በፈተና ውጤታቸው መካከልመካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን ጥናቱ አረጋግጧል።ከዚህ እንደምንረዳው ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ቀና አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉና ለአማርኛ ቋንቋ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ውጤታቸው አነስተኛ እንደሚሆን ጥናቱ አመላክቷል።

## 4.3. የጥናቱ ማብራሪያ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያለውንዝምድናእንዲሁም በሴትና በወንድ ተማሪዎች መሀከል ያለውን የአመለካከት ልዩነት መመርመር ነው ።ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሰነድ ፍተሻና በጹሁፍ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቦ ውጤቱ በስታስቲካዊ ትንታኔ ታይቷል።

በመሆኑም በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የተለያዩ ምሁራን ካቀረቡትየንድፈ ሀሳብና የጥናት ውጤቶች ጋር በማዛመድ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር በሚገኘው ምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ 10ኛክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ባላቸው አመለካከት ላይ በተሰራው ጥናት የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የአመለካከት አማካይስሌት 2.755 እንደሆነ ተረጋግጧል። ይህ ውጤት ኪትጃሮንይ፣2013፣ገጽ26 ላይ በተገለፀው የአመለካካት

ወሰን መሰረት አመለካከት (ከ2–2.99)መሀከል ከሆነ የአመለካከት ደረጃው አሉታዊ መሆኑን ተገልጿል። በመሆኑም ይህ የተገኘው የአመለካከት አማካይ ውጤት (2.755) ከላይ በተገለፀው የአመለካከት ወሰን ውስጥ በመሆኑተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋና ትምህርትአሉታዊ አመለካከት እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል።ይህ በተለያዩ ምሁራን የጥናት ውጤቶችም ላይ ተረጋግጧል ። **ለምሳል** Medhanie (1986) and Mohamed (2004) ፀጋዬ (1996) ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋለመማርያላቸውአመለካከት አሉታዊ መሆኑን አመላክተዋል።

ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከፆታ አንፃር ልዩነት ይኖረው እንደሆነ ለማት የተሞከረ ሲሆን የሴት ተማሪዎች አማካይ የአመለካከት ውጤት 2.8080 እንዲሁም የወንድ ተማሪዎች አማካይ የአመለካከት ውጤት 2.755 መሆኑን ከተተነተነው መረጃ ለማየት ተችሏል:: በመሆኑም የተገኘው አማካይ የአመለካከት ውጤት በተመሳሳይ የአመለካከት ወስን **(2.00–2.99)**መካከል የሚገኝ በመሆኑ የሁለቱም ፆታ አመለካከት አሉታዊሆኖ ተገኝቷል ። በመሆኑ ከአመለካከት አንጻር በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል። ይሁን እንጂ በሴቶች አመለካከት አማካይ ውጤትና በወንዶች አመለካከት አማካይ ውጤት ጥቂት ልዩነት መኖሩንና አሉታዊነቱ የሴቶች ያነሰ መሆኑን ግኝቱ አመላክቷል ። ይህ ግኝት Bacon (1992) ፤ (Akram & Ghani, 2013) ሁለተኛ ቋንቋ ከመማር አኳያ በጾታ መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ በጥናታቸው ካገኙት ውጤት ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ሌሎችምሁራንማለትም Gardner and Lambert (1972) ፤ Spolsky (1989) ካጠኑት ሴት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ከወንዶች የበለጠ አዎንታዊ አመለካከት እንዳላቸው ካረጋገጡት የጥናት ውጤት ጋር አይገናኝም።

ሌላኛው የዚህ ጥናት ዓላማ በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ምን ዓይነት ዝምድና እንዳለ መፈተሽ ነበር። በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየውበአመለካከትና በተማሪዎች ውጤት መካከል ያለው ዝምድና0.456 መሆኑንስሌቱ

አሳይቷል ።ይህ የተዛምዶ ውጤት ከተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል መካከለኛ ዝምድና መኖሩንያሳያል። ይኸውም ቋንቋውን ለመማር አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤትን ሲያስመዘግቡ በአንፃሩ ደግሞ ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች የተሸለ ውጤት እንደሚኖራቸው በጥናቱ ታይቷል።ይህ የጥናት ውጤት በሌሎች የጥናት ውጤትም ተረጋግጧል። ለአብነትም Karaş (1997), ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ባላቸው አመለካከትና በፈተና ውጤታቸው መሀከል አዎንታዊ ግንኙነት መኖሩን በማመላከትግንኙነቱ ጠንካራ አለመሆኑን ካረጋገጠው የጥናት ውጤት ጋርግንኙነት አለው።

በመጨረሻም የሴት እና ወንድ ተማሪዎችንየአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት የማነፃፀር ስራ ተሰርቷል ። በዚሁ መሰረት የሴት ተማሪዎች አማካይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት 54.62 ሲሆን የወንድ ተማሪዎች አማካይ የአማርኛ ቋንቋውጤት 52.36 ሆኗል። ይህም የአማካይ ውጤት ልዩነት የተፈጠረው ሴቶች ከወንዶች ያነሰ አሉታዊ አመለካከት ስላላቸው ሊሆን እንደሚችል አጥኚዋአስተውላለች

# ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ

## 5.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ላይ የተከናወነ ነው ፡፡ጥናቱም የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የውጤት ተዛምዶ መመርመርን ዓላማ አድርጎ የተነሳ ነው፡፡በዚህም የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በመመለስ ላይ አተኩሯል፡፡

1. በሲዳምኛ ቋንቋ አፈፊት የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት መመርመር፡፡
2. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፆታ አንጻር ልዩነት እንዳለው መመርመር
3. በተማሪዎች አመለካከትና በውጤታቸው መካከል ምን ዓይነት ዝምድና እንዳለ መፈተሽ

ለጥያቄዎችም መልስ ለመስጠት አጥኚዋ የተለያዩ የጥናት ዘዴዎችን እና መሳሪያዎችን ተጠቅማለች፡፡ ለጥናቱ ከምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል ከሚማሩና አፍ መፍቻቸው ሲዳምኛ ከሆኑ በዕኩል ዕድል ሰጪ የናሙና አመራረጥ ስልት 103 ተማሪዎች በተጠኚነት ተመርጠዋል ፡፡

ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት ከአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ዝምድና ለማወቅ አመለካከትን የሚለካ የፅሁፍ መጠይቅ የተለያዩ ሊቃውንት ያዘጋጁትን የአመለካከት መለኪያ መጠይቆችን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡ መጠይቁም በሁለት የትምህርት ባለሙያዎችና በጥናቱ አማካሪ ታይቷል ፡፡ የመጠይቆችን አስተማማኝነት ለመፈተሽም የመስክ ጥናት ተከናውኖ በክሮምባች /crombach Alpha/ ቀመር መሰረት 0.815 መሆኑ ተረጋግጧል ፡፡

የተማሪዎች የፈተና ውጤትን በተመለከተ ከተገቢነት አንፃር የአንድ የምዘና ወይም የፈተና ዉጤት ብቻ ወስዶ ከማስላት ይልቅ ተከታታይ የአንደኛ መንፈቀ ዓመት ፈተና ዉጤት ድምር ተወስዷል፡፡

የተማሪዎች አመለካከት በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት ከተሰበሰበ በኋላ ተማሪዎቹ ካስመዘገቡት ውጤት ጋር እየተዛመደ ተመዝግቧል፡፡ በመቀጠል የተማሪዎቹ አጠቃላይ የአመለካከትና ውጤት አማካይ ከቀረበ በኋላ በፒርሰን ተዛምዶ /Pearson correlation/ መለኪያ መሰረት በአመለካከትና ውጤት መካከል ያለው ዝምድና ታይቷል፡፡ በአመለካከትና ውጤት መካከል ያለው ዝምድናም 0.456 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም በአመለካከትና ውጤት መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ዜዴዎችና ስሌት መሰረት የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝቷል፡፡

በሲዳምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ከፆታ አንፃር ልዩነት የጎላ ልዩነት እንደሌለው ተረጋግጧል፡፡

የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ የሆኑ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት መካከል መካከለኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና በትምህርቱ ያስመዘገቡት ውጤት በፒርሰን ተዛምዶ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው አብዛኞቹ ተማሪዎች ከአማካይ በታች ያስመዘገቡ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ይህም የአብዛኞቹ ተማሪዎች ውጤት

ከአማካይ በታች መሆን በጥናቱ ውጤት እንደተረጋገጠው ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ትምህርቱ ያስመዘገቡት አመለካከት አሉታዊ ከመሆን ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

## 5.2. አስተያየት

ከላይ በቀረቡት የጥናቱ ውጤቶች ላይ በመመስረት አጥኚዋ የሚከተለውን አስተያየት ትሰነዝራለች

1. ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በሚማሩበት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ እንዲሆን መምህራን የራሳቸውን ፈጠራ በመጠቀም የትምህርት ይዘት አመራረጥና የማስተማር ስነ ዘዴን ከተማሪዎች ተነሳሽነትና ፍላጎት እንዲሁም ከታላሚው ቋንቋ ባህል ጋር በማስማማት እና ተጨባጭ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አደራጅቶ በመተግበር አሳታፊ የሆነ የመማር ማስተማር ክንውንን በማስፈን ለተማሪዎች አመለካከት አዎንታዊ መሆን ተግቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡
2. ት/ቤቶች በተማሪዎች አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖዎች የሚቀረፉበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና መተግበር ያስፈልጋል፡፡

3. አመለካከት ሲጨምር ውጤት እንደሚጨምር አመለካከት ሲቀንስ ውጤት እንደሚቀንስ ጥናቱ አመላክቷል ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች ውጤት ማነስ ከአሉታዊ አመለካከት ጋር የተያያዘ በመሆኑ አዎንታዊ አመለካከትን በሚያሰርፁ ተላዉጠዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸውና ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል

4. ወደፊት የሚዘጋጀው ስርዓተ ትምህርት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ቀና አመለካከት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ተላውጦዎችን በማካተት ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

# ዋቢ መፅሃፍት


ተዋበች ተክሌ ። (2003) ። ‹‹የአፍ መፈቻ ቋንቋቸዉ ከፍኛ የሆኑ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸዉ አመለካከትና የፈተና ዉጤታቸዉ ዝምድና ። ››አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ያልታተመ)።

ታሪኩ ፋንታዬ። (1988)። ‹‹የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርትላይ ያላቸው አመለካከት። ››አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ (ያልታተመ)።

አበበ ከበደ። (2003) ። ‹‹የመሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸዉ አመለካከትና በዉጤታቸዉ መካከል ያለዉ ዝመድና። ››አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ (ያልታተመ)።

እሸቱ ወንድሙ። (1997)። ‹‹ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለመማር ባላቸዉ ፍላጎትና በዉጤታቸዉ መካከል ያለ ግንኙነት በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ትምህርት ቤት የተካሄደ ጥናት። ››አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ (ያልታተመ)።

ወንደሰን በየነ። (1989) ። ‹‹የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲየኛ የሆነ የአስራሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና። ››አዱስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጹሁፍ፣ (ያልታተመ)።

ፀጋዬ አረጋይ። (1996)። ‹‹ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በሚኖራቸዉ አመለካከት ላይ ዝምድና ያላቸዉ ተላዉጦዎች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የተካሄደ ጥናት። ››አዲስ አበባ፣ በቋንቋዎች ተቋም ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ (ያልታተመ)።

Akram, M., & Ghani, M. (2013).*Gender and Language Learning Motivation. Academic Research International*

Asher, R. E., & Simpson, J. M. Y. (1994). *Attitude Surveys: Question-AnswerProcess. The Encyclopedia of Language and Linguistics.*

Boonrangsri, K., Chuaymankhong, D., Rermyindee, N., & Vongchittpinyo, N. (2004).The *Attitude towards English language learning of the Students in Vocational Certificate level under Curriculum in 2002. A Case Study of Ayutthaya Technical College Studied by Naresuan University, Thailand.*

Cohen, J. (1988) *Statistical Power Analysis for the Behavioral Sciences, 2nd ed. Hillsdale, NJ: Erlbaum*.

Crew, V. (1994b). *When does a Carrot Become a Stick? Changing Attitudes and English Language Proficiency of Hong Kong Students Teachers*.

Dörnyei, Z., & Ottó, I. (1998). *Motivation in action: A process model of L2 motivation.*

Dörnyei, Z. (2006). *Individual differences in second language acquisition*

Dubin Fraida and Elite oshtain. (1986*).Course Design Site Developing Programs and Material for Language Learning.*

Ellis, R. (1994). *The Study of Second Language Acquisition*.

Fernald, L. Dand Peter, S. F. (1999*). Introduction to Pychology*. *5thed*. Delhi: A.I.T.B.S publishers and Distributors.

Gardner, R. C. (2005). *Integrative Motivation and Second Language Acquisition.*

Gardner, R. C., & Lambert E. W. (1972).*Attitudes and Motivation in SecondLanguage Learning*.

Gardner, R.C.(1985). *Social Psychology and Second Language Learning.The role of Attitude and Motivation.*

Lambert, W. E. (1974).*Culture and Language as Factors in Learning and Education*.

Lanara, S. (1999), *Attitudes and Motivation of Japanese Students Studying English at Asia University*

Harmer, Termy.(1983). *The Practice of English Language Teaching*.NewYork :Long Man.(1990). The Practice of English Language Teaching**.**NewYork LongMan Group ltd

Hoover.K.H&M Hollingworth(1995) *learning & teaching Elementry school.Boston:Allgh& Becom,I nc*

Hurlock, E.B.(1996). *Developmental Psychology a Life Spans Approch***.** 8thed. Delhi McGraw-Hill Publishing Company Ltd.

Karaş M. (1996), *Using Attitude Scale to Investigate Student Attitude*, (paper presentation). 2. IATEFL Balkan ELT Konferansı. İstanbul 5-7 Eylül.

Kitjaroonchai, N. (2013). *Motivation toward English Language Learning of Students in Secondary and High Schools in Education Service*

Malim,T.andAnn,Birch.(1998).,Introductry Psychology,London:Macmillanpress Ltd

Mansoor, S. (1993). *Punjabi, Urdu, English in Pakistan: A sociolinguistic Study*.

Masgoret, A-M., & Gardner, R. C. (2003) *Attitudes, Motivation, and Second Language Learning*: A meta-analysis of Studies Conducted by Gardner and Associates.

Medhanie, H. (1986). The *Attitude of Grade Eleven Students towards Learning English* [Unpublished MA Thesis]. Addis Ababa University. [Google Scholar]

Mclaughlin, Barry. (1991). *Theories of second Language. Landon:* Edward Amold. Murciacelese maarinne(ed). (1991). *Teaching English as a Second Language Foreign Language*.

Mohamed, K. (2004). *The Attitude of Year one Preparatory Students towards Learning English as a Foreign Language* [Unpublished MA Thesis]. Addis Ababa University.

*Montano, D,. E. & Kasprzyk, D. (2008).* Theory of Reasoned Action, Theory ofPlanned Behavior, and The Integrated Behavioral model.

Nunan D.C Lanbert.(1996).*The Self Directed Teacher. Cambridge: Cambride University Press*.

Redy and Bergerman.(1995). *In The Classroom an Introduction to Education* NewYork Dustinkinpub**.**Groupinc**.**

Roger,D,and Peter,H,(1995),*Mastering Psychology 2nd ed.London*:Macmillan Press

Rosenberg and Howland.(1980). << *Cognitive, Affective, and behavioral Components of Attitude*>> in M. J. Rosenberg etal (eds Attitude Organization and change.

Saracaloğlu, (1995) Revealed the same Finding with Yaşar (1989) That *Male Students have More Favorable Attitude than Female Students*

Shelden,E.(1987).ELTTex Books and Materials: *problems in Evaluation Development*.London: modernEnglish pblishers.

Spolskey, Bernard. (1989). <<*Attitudinal Aspects of Second Language Learning.*>> Jornal of Applied Linguistics language larning vol.19.No.3

TaronE.GYale,*Focuses on the language Learning*.London:oxford universe press

Tremblay, P. F., & Gardner, R. C. (1995). *Expanding the Motivation Construct in Language Learning.*

Umre & Kamil.(2012). *Analysis of the Relationship Between Reading and Writing Attitudes of Teacher Candidates and Academic Achievements Throught the Structural Equation Model*.

Wu, K. –H. (2010). *The Relationship Between Language Learners'Anxiety and Learning Strategy in the CLT Classrooms*.

Youssef, S. M. (2012). *Role of Motivation and Attitude in Introduction and Learning of English as a Foreign Language in Libyan High Schools.*

## የፅሁፍ መጠይቅ “

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂውማኒቲስ. ቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

# የአማርኛ ትምህርት ክፍል

### ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

***የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ በሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ***

***የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ*** *በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ምስራቅ ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲዳምኛ በሆኑ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋና ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የውጤት ዝምድናን ለማጥናት የሚያገለግል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚያገለግል ሲሆን ውጤቱም ለተማሪዎች ለመምህራን ለትምህርት አዘጋጆች ጥቅም ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎችን በትክክል አንብበህ/ሽ ትክክለኛውን መልስ እንድትሞላ/ይ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡*

***መመሪያ***

1. *መጠይቁ ሲሞላ ስም መፃፍ አያስፈልግም*
2. *ለመጠይቁ የሚሰጠው መልስ በሚሰጥር መያዝ አለበት*
3. *የጥናቱ ውጤት ከተፈለገው አላማ ይደርስ ዘንድ ሃሳባችሁን በነጻ ፍላጎት እንድትሞሉ ትጠየቃላችሁ*
4. *ጥያቄዎቹና መልሶቹ ለተጠቀሰው አላማ በስተቀር ለሌላ አላማ እንደማይውሉ ማወቅ ያስፈልጋል*
5. *የመጠይቁ አሞላል ስልት እያንዳንዱ ጥያቄ ፊት ለፊት አምስት አማራጭ መልሶች ስለተሰጡ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ቁጥር የ x ምልክት በማድረግ ማረጋገጥ ይገባል፡፡*

አማራጭ መልሶቹ ለአንድ ጥያቄ ከቀረቡት ውስጥ ሁለቱ “የመስማማትን” ሁለቱ ደግሞ “አለመስማማትን” ሃሳብ የያዙ ሲሆን አንዱ ደግሞ የመስማማትንም ሆነ ያለመስማማትን “ሃሳብ ለመስጠት መቸገርን” የያዘ ነው፡፡

የመስማማትንም ሆነ ያለመስማማትን ሃሳብ የያዙት አማራጮች በጥያቄው መንፈስ ላይ “በጣም መስማማትን” ወይም “በመጠኑ መስማማትን” የሚጠቁሙና በደረጃ የሚያስቀምጡ ሲሆኑ በተቃራኒ ያሉትንም እንደዚሁ በጥያቄው ላይ “በመጠኑ አለመስማማትን” እና “ፍፁም አለመስማማትን “የሚያማርጡ በመሆናቸው በጥያቄው ላይ ያለውን የመስማማት ወይም አለመስማማት ደረጃን በመወሰን መልስ እንዲሰጥበት ያስፈልጋል::

አጥኚዋ ለሚደረግላት ትብብርና ለሚሞላው ትክክለኛ ሃሳብ በቅድሚያ ታመሰግናለች፡፡

**<u>ክፍል አንድ</u>፡- የፅሁፍ መጠይቅ መላሽ ግለሰብ ጥሬ መረጃ**

**ከዚህ በታች በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ  ትክክለኛውን መረጃ ሙላ/ይ**

1. ፆታ -----------
2. ዕድሜ----------
3. የክፍል ደረጃ--------
4. ብሄረሰብ-------------
5. የአፍ መፍቻ ቋንቋ------------

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ለእያንዳንዱ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመስፈርቱ መሰረት በሰንጠረዡ የተቀመጡትን ቁጥሮች በመክበብ ይመልሱ ፡፡

**<u>መመዘኛ</u>**፡- 1 ፈፅሞ አልስማማም 2 አልስማማም  3 ለመወሰን እቸገራለሁ 4  እስማማለሁ 5  በጣም እስማማለሁ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በማንኛውም ቦታ አማርኛ ቋንቋን መናገር ያስጨንቀኛል ፡፡ | | | | | |
| 2 | አማርኛ ቋንቋን መማር ከጓደኞቼ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረኝ ይረዳኛል፡፡ | | | | | |
| 3 | አማርኛ ቋንቋን መማር የግል ስብዕናዬን እንዳሻሽል ይረዳኛል ፡፡ | | | | | |
| 4 | የተሰጠኝን የአማርኛ ቋንቋ የቤት ስራ ፈጥኖ የመስራት ተነሳሽነት የለኝም ፡፡ | | | | | |
| 5 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አማርኛ ቋንቋን መናገር ነፃነት አይሰጠኝም ፡፡ | | | | | |
| 6 | በሌሎች ተማሪዎች ፊት አማርኛ ቋንቋን ለመናገር ሀፍረት ይሰማኛል፡፡ | | | | | |
| 7 | አማርኛ ቋንቋን እንደ ቋንቋው ባለቤት ተናጋሪዎች መናገርን እወዳለሁ፡፡ | | | | | |
| 8 | የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሲያመልጠኝ በዕለቱ በቀረበው ትምህርት ላይ የተሰጠውን የቤት ስራ ጋደኞቼንም ሆነ መምህሬን በፍፁም አልጠይቅም፡፡ | | | | | |
| 9 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ወደ ክፍል መግባት አያጓጓኝም ፡፡ | | | | | |
| 10 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ መሆን የተለያዩ መፅሀፍትን በሚገባ ለማንበብ ይረዳኛል፡፡ | | | | | |
| 11 | እውነት ለመናገር አማርኛ ቋንቋን የማጠናው ፈተና ለማለፍ ነው፡፡ | | | | | |
| 12 | በኔግምት ከአንድ ቋንቋ በላይ የሚናገሩ ሰዎች ብዙ እውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ | | | | | |
| 13 | አማርኛ ቋንቋን ማወቅ ጥሩ ተናጋሪ እንድሆን ያስችለኛል ፡፡ | | | | | |
| 14 | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዕውቀት በእለት ከዕለት ኑሮዬ የምጠቀምባቸው አይደሉም ፡፡ | | | | | |
| 15 | አማርኛ ቋንቋን መማር አዳዲስ ሀሳቦችን እንድፈጥር ይረዳኛል ፡፡ | | | | | |
| 16 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለኝ ብቃት የሚያረካ አይደለም፡፡ | | | | | |
| 17 | በኔ ግምት አማርኛ ቋንቋን መማር አስቸጋሪና ውስብስብ ነው፡፡ | | | | | |
| 18 | አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ብዙ የእውቀት መስኮችን የሚሸፍን ይዘት አለው፡፡ | | | | | |
| 19 | ከሁለተኛ ቋንቋ ይልቅ በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ መማርን እመርጣለሁ ፡፡ | | | | | |
| 20 | እውነት ለመናገር ለአማርኛ ክፍለ ጊዜ ያለኝ ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ | | | | | |
| 21 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ጥያቄዎችን ስመልስ ምንም ዓይነት ጭንቀት አይሰማኝም ፡፡ | | | | | |
| 22 | አማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋዬ ቢሆንም መማር ያስደስተኛል ፡፡ | | | | | |
| 23 | አማርኛ ቋንቋን በመማሬ ኩራት ይሰማኛል፡፡ | | | | | |
| 24 | አማርኛ ቋንቋን መማር በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማኝ ያደርገኛል፡፡ | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | አማርኛ ቋንቋን የማወቅ ፍላጎት አለኝ። | | | | | |
| 26 | አማርኛ ቋንቋን ማወቅ በህይዎቴ ለማሳካት የምፈልገው ግቤ ነው። | | | | | |
| 27 | የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜን የማሳልፈው በደስታ ነው። | | | | | |
| 28 | አማርኛ ቋንቋን መማሬ ጥሩ ስሜት እንዲኖረኝ አድርጎኛል ። | | | | | |

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ ፡ የአንደኛ መንፈቅ ዓመት የተማሪዎች ውጤትእና አማካይ የአመለካከት ውጤት

| ተ.ቁ | የአንደኛ መንፈቅ ዓመት የተማሪዎች ውጤት | አማካይ የአመለካከት ውጤት |
|---|---|---|
| 1 | 48 | 2.25 |
| 2 | 41 | 2.43 |
| 3 | 65 | 3 |
| 4 | 56 | 3.14 |
| 5 | 42 | 2.39 |
| 6 | 45 | 3.11 |
| 7 | 38 | 2.79 |
| 8 | 49 | 2.57 |
| 9 | 48 | 2.43 |
| 10 | 46 | 2.43 |
| 11 | 49 | 2.07 |
| 12 | 44 | 1.93 |
| 13 | 46 | 2.14 |
| 14 | 44 | 2.86 |
| 15 | 34 | 2 |
| 16 | 45 | 2.18 |
| 17 | 47 | 3.04 |
| 18 | 46 | 2.39 |
| 19 | 47 | 2.5 |
| 20 | 45 | 2.96 |
| 21 | 46 | 2.86 |
| 22 | 46 | 1.93 |
| 23 | 50 | 2.39 |
| 24 | 51 | 2 |
| 25 | 39 | 3.11 |
| 26 | 41 | 2.39 |
| 27 | 48 | 2.89 |
| 28 | 39 | 2.36 |
| 29 | 40 | 2.86 |

| ተ.ቁ | የአንደኛ መንፈቅ ዓመት የተማሪዎች ውጤት | አማካይ የአመለካከት ውጤት |
|---|---|---|
| 30 | 57 | 2.86 |
| 31 | 58 | 2.29 |
| 32 | 65 | 3.07 |
| 33 | 56 | 2.75 |
| 34 | 42 | 2.93 |
| 35 | 54 | 3.04 |
| 36 | 36 | 2.32 |
| 37 | 43 | 2.93 |
| 38 | 51 | 3 |
| 39 | 51 | 2.32 |
| 40 | 53 | 2.93 |
| 41 | 34 | 2.79 |
| 42 | 47 | 2.32 |
| 43 | 57 | 2.39 |
| 44 | 42 | 2.57 |
| 45 | 49 | 2.68 |
| 46 | 48 | 2.39 |
| 47 | 47 | 3 |
| 48 | 57 | 3.18 |
| 49 | 68 | 3.54 |
| 50 | 50 | 2.5 |
| 51 | 51 | 2.43 |
| 52 | 49 | 2.82 |
| 53 | 58 | 3.29 |
| 54 | 57 | 3.32 |
| 55 | 50 | 3.14 |
| 56 | 51 | 3.11 |
| 57 | 64 | 3.18 |
| 58 | 46 | 2.57 |
| 59 | 50 | 3.07 |
| 60 | 49 | 2.68 |
| 61 | 55 | 2.68 |
| 62 | 52 | 2.61 |

| ተ.ቁ | የአንደኛ መንፈቅ ዓመት የተማሪዎች ውጤት | አማካይ የአመለካከት ውጤት |
|---|---|---|
| 63 | 50 | 2.71 |
| 64 | 60 | 3.14 |
| 65 | 58 | 2.82 |
| 66 | 67 | 3.39 |
| 67 | 52 | 3.04 |
| 68 | 57 | 3.29 |
| 69 | 62 | 3.11 |
| 70 | 62 | 3.39 |
| 71 | 46 | 2.29 |
| 72 | 50 | 2.75 |
| 73 | 49 | 2.46 |
| 74 | 50 | 2.86 |
| 75 | 53 | 3.11 |
| 76 | 56 | 2.86 |
| 77 | 62 | 2.54 |
| 78 | 56 | 2.71 |
| 79 | 61 | 2.32 |
| 80 | 56 | 2.32 |
| 81 | 67 | 2.79 |
| 82 | 85 | 2.89 |
| 83 | 61 | 2.68 |
| 84 | 59 | 3.43 |
| 85 | 59 | 3.32 |
| 86 | 87 | 3.64 |
| 87 | 49 | 3.18 |
| 88 | 79 | 3.46 |
| 89 | 80 | 3.43 |
| 90 | 49 | 3.14 |
| 91 | 60 | 2.68 |
| 92 | 65 | 2.5 |
| 93 | 50 | 2.21 |
| 94 | 76 | 2.89 |
| 95 | 58 | 2.36 |

| ተ.ቁ | የአንደኛ መንፈቅ ዓመት የተማሪዎች ውጤት | አማካይ የአመለካከት ውጤት |
|---|---|---|
| 96 | 69 | 2.54 |
| 97 | 57 | 2.54 |
| 98 | 53 | 2.18 |
| 99 | 60 | 3 |
| 100 | 75 | 2.89 |
| 101 | 80 | 2.93 |
| 102 | 54 | 2.96 |
| 103 | 52 | 3 |

**mid term result**

| result | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 34 | 2 | 1.9 | 1.9 | 1.9 |
| | 36 | 1 | .9 | 1.0 | 2.9 |
| | 38 | 1 | .9 | 1.0 | 3.9 |
| | 39 | 2 | 1.9 | 1.9 | 5.8 |
| | 40 | 1 | .9 | 1.0 | 6.8 |
| | 41 | 2 | 1.9 | 1.9 | 8.7 |
| | 42 | 3 | 2.8 | 2.9 | 11.7 |
| | 43 | 1 | .9 | 1.0 | 12.6 |
| | 44 | 2 | 1.9 | 1.9 | 14.6 |
| | 45 | 3 | 2.8 | 2.9 | 17.5 |
| | 46 | 7 | 6.6 | 6.8 | 24.3 |
| | 47 | 4 | 3.8 | 3.9 | 28.2 |
| | 48 | 4 | 3.8 | 3.9 | 32.0 |
| | 49 | 8 | 7.5 | 7.8 | 39.8 |
| | 50 | 8 | 7.5 | 7.8 | 47.6 |
| | 51 | 5 | 4.7 | 4.9 | 52.4 |
| | 52 | 3 | 2.8 | 2.9 | 55.3 |
| | 53 | 3 | 2.8 | 2.9 | 58.3 |
| | 54 | 2 | 1.9 | 1.9 | 60.2 |
| | 55 | 1 | .9 | 1.0 | 61.2 |
| | 56 | 5 | 4.7 | 4.9 | 66.0 |
| | 57 | 6 | 5.7 | 5.8 | 71.8 |
| | 58 | 4 | 3.8 | 3.9 | 75.7 |
| | 59 | 2 | 1.9 | 1.9 | 77.7 |
| | 60 | 3 | 2.8 | 2.9 | 80.6 |
| | 61 | 2 | 1.9 | 1.9 | 82.5 |
| | 62 | 3 | 2.8 | 2.9 | 85.4 |
| | 64 | 1 | .9 | 1.0 | 86.4 |
| | 65 | 3 | 2.8 | 2.9 | 89.3 |
| | 67 | 2 | 1.9 | 1.9 | 91.3 |
| | 68 | 1 | .9 | 1.0 | 92.2 |
| | 69 | 1 | .9 | 1.0 | 93.2 |
| | 75 | 1 | .9 | 1.0 | 94.2 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 76 | 1 | .9 | 1.0 | 95.1 |
| | 79 | 1 | .9 | 1.0 | 96.1 |
| | 80 | 2 | 1.9 | 1.9 | 98.1 |
| | 85 | 1 | .9 | 1.0 | 99.0 |
| | 87 | 1 | .9 | 1.0 | 100.0 |
| | Total | 103 | 97.2 | 100.0 | |
| Missing | System | 3 | 2.8 | | |
| Total | | 106 | 100.0 | | |

**attitude**

| Mean score | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 1.93 | 2 | 1.9 | 1.9 | 1.9 |
| | 2.00 | 2 | 1.9 | 1.9 | 3.9 |
| | 2.07 | 1 | .9 | 1.0 | 4.9 |
| | 2.14 | 1 | .9 | 1.0 | 5.8 |
| | 2.18 | 2 | 1.9 | 1.9 | 7.8 |
| | 2.21 | 1 | .9 | 1.0 | 8.7 |
| | 2.25 | 1 | .9 | 1.0 | 9.7 |
| | 2.29 | 2 | 1.9 | 1.9 | 11.7 |
| | 2.32 | 5 | 4.7 | 4.9 | 16.5 |
| | 2.36 | 2 | 1.9 | 1.9 | 18.4 |
| | 2.39 | 6 | 5.7 | 5.8 | 24.3 |
| | 2.43 | 4 | 3.8 | 3.9 | 28.2 |
| | 2.46 | 1 | .9 | 1.0 | 29.1 |
| | 2.50 | 3 | 2.8 | 2.9 | 32.0 |
| | 2.54 | 3 | 2.8 | 2.9 | 35.0 |
| | 2.57 | 3 | 2.8 | 2.9 | 37.9 |
| | 2.61 | 1 | .9 | 1.0 | 38.8 |
| | 2.68 | 5 | 4.7 | 4.9 | 43.7 |
| | 2.71 | 2 | 1.9 | 1.9 | 45.6 |
| | 2.75 | 2 | 1.9 | 1.9 | 47.6 |
| | 2.79 | 3 | 2.8 | 2.9 | 50.5 |
| | 2.82 | 2 | 1.9 | 1.9 | 52.4 |
| | 2.86 | 6 | 5.7 | 5.8 | 58.3 |
| | 2.89 | 4 | 3.8 | 3.9 | 62.1 |
| | 2.93 | 4 | 3.8 | 3.9 | 66.0 |
| | 2.96 | 2 | 1.9 | 1.9 | 68.0 |
| | 3.00 | 5 | 4.7 | 4.9 | 72.8 |
| | 3.04 | 3 | 2.8 | 2.9 | 75.7 |
| | 3.07 | 2 | 1.9 | 1.9 | 77.7 |
| | 3.11 | 5 | 4.7 | 4.9 | 82.5 |
| | 3.14 | 4 | 3.8 | 3.9 | 86.4 |
| | 3.18 | 3 | 2.8 | 2.9 | 89.3 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 3.29 | 2 | 1.9 | 1.9 | 91.3 |
| | 3.32 | 2 | 1.9 | 1.9 | 93.2 |
| | 3.39 | 2 | 1.9 | 1.9 | 95.1 |
| | 3.43 | 2 | 1.9 | 1.9 | 97.1 |
| | 3.46 | 1 | .9 | 1.0 | 98.1 |
| | 3.54 | 1 | .9 | 1.0 | 99.0 |
| | 3.64 | 1 | .9 | 1.0 | 100.0 |
| | Total | 103 | 97.2 | 100.0 | |
| Missing | System | 3 | 2.8 | | |
| Total | | 106 | 100.0 | | |

## ለጥናታዊፅሁፍ የተሳታፊ ፍቃድ መጠየቂያ ቅፅ

እኔ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማስተርስተማሪነኝ፡፡

ይህንን የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች በማሟላት የጥናት ፅሁፍ እየሰራሁ ነው፡፡ የእርስዎ ተሳትፎ ከአንድ እስከ ሁለት ሰአታት መካከል የሚቆዩ የፅሁፍ መጠይቆችን መሙላት ነው፡፡ ምቾት እንዳይሰማዎት የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ላለመመለስ ነፃ ነዎት፡፡ መጠይቁን አለመሙላት ምንም ቅጣት የለውም፣እንዲሁም ለተሳትፎዎ ምንም ስጋት አይኖረውም፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት በዚህ መስክ ላሉ ባለሙያዎች ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡እንዲሁም ተማሪዎች አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማር እንዲችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ይረዳል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ጥናት ለባህል መሪዎች፣ፖሊሲ አውጪዎች፣ተመራማሪዎች እና በትልቁ ለማህበረሰቡ በተለያዩ መንገዶች ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ የማስተርስ ዲግሪዬን ለመፃፍ እና ለመጨረስ ይረዳኛል፡፡

ለማንኛውም ጥያቄዎች፣እባክዎን ተመራማሪውን ሀዋሳ ከ/አስተዳደር ምስራቅ ጮራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛ ዲፓርትመንት ያነጋግሩ፡፡

ከዚህ በታች በመፈረም ከላይ ያለውንመረጃ ተረድቼ የጥናቱ አካል ለመሆን ፈቃዴን ሰጥቻለሁ፡፡

ፊርማ................................ቀን..................................................